# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 206 መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በሳውዲ ዓረቢያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ዜጎችን የመመለሱ ተግባር ተጠናቀቀ

## - በአንድ አመት ውስጥ ከ131ሺ በላይ ዜጎች ወደ አገራቸው ተመልሰዋል


**ፋንታነሽ ክንዴ**


አዲስ አበባ፡- በሕገወጥ መንገድ ከአገር ወጥተው በሳውዲ ዓረቢያ በእስር ላይና በማቆያ ቦታዎች በችግር ውስጥ የነበሩ ዜጎችን ወደ አገራቸው የመመለስ ሥራ ተጠናቀቀ። ከመጋቢት 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከ131 ሺህ በላይ ዜጎች ወደአገራቸው መመለሳቸውም ተጠቁሟል።

በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው ከስደት ተመላሾችን የተቀበሉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታና የሳውዲ ስደተኞችን ለመመለስ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ሰብሳቢ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ እንደገለጹት፤ መጋቢት 21 ቀን 2014 ዓ.ም ሕገወጥ ስደተኞችን የመመለሱ ተግባር


**በሳውዲ ዓረቢያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# የኢትዮጵያና የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማዎች ግንኙነታቸውን እንደሚያጠናክሩ አስታወቁ


**ጌትነት ተስፋማርያም**


አዲስ አበባ፡- የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ፍላጎት እንዳላቸው አስታወቁ።

የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማ ልዑክ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና አባላት ጋር ትናንትና ውይይት አድርጓል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ዲማ ነገዎ፤ በኢትዮጵያና ዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከርና በቀጣይ ሊኖሩ ስለሚገባቸው የትብብር ሥራዎች መንደርደሪያ የሚሆን ውይይት መካሄዱን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያና ዩናይትድ ኪንግደም ከ19ኛው ክፍለ


**የኢትዮጵያና የዩናይትድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**




ፎቶ - ኢዮብ ተፈሪ





የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

የሚሰጡ አገልግሎቶች
- ለቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎት አቅራቢዎች ፈቃድ መስጠት
- የቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎቶችን መቆጣጠር
- የፍሪኩዌንሲ እና የቴሌኮም ቁጥር ሀብቶችን ማስተዳደር
- የቴሌኮም መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቅሬታ መፍታትና መብት ማስጠበቅ
- የዘርፉን ፍትሃዊ ተወዳዳሪነት ማበረታታት
- ሁሉን አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ታሪፍ መቆጣጠር

አድራሻ ከኤድናሞል ወረድ ብሎ ሮቤል ፕላዛ ህንፃ
+251-11-692-80-42 | contact@eca.et
9991 | https://www.eca.et

ጥራት ያለው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ እንጥራለን!




# በክልሉ በማዕድን ልማት ፈቃድ ከወሰዱ ከ250 በላይ አልሚዎች ውስጥ 20ዎቹ ብቻ ወደ ሥራ ገብተዋል

- 45 የውጭ አገራት ሕገወጥ የወርቅ አዘዋዋሪዎችም በቁጥጥር ስር ውለዋል


ገጽ 4


# «በኤሌክትሪክ መቆራረጥ ምክንያት ለአራት ዓመታት ተቸግረናል»

- የዳዬ ከተማ ነዋሪዎች

# «ችግሩ በሁለት ወራት ውስጥ ይፈታል»

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሲዳማ ሪጅን


ገጽ 4





ዜና

# በቦረና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የውሃ ችግርን ለማቃለል እየተሠራ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በቦረና የዝናብ ውሃን በማጠራቀም በዘመናዊ መንገድ ዳግም አገልግሎት ላይ የሚውልበትን መንገድ ለመፍጠር እና በየቤቱ ያለውን የውሃ ችግር ለማቃለል በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። በአሁኑ ወቅትም በቦረና 40 ሴቶችን በማደራጀት 200 ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ የሚያስችል ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ታመነ ኃይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ውሃን ከመኖሪያ ቤት ጣሪያ ላይ በመያዝ መሬት ስር ወደሚቀበረው ማጠራቀሚያ በማስገባት መጠቀም የሚቻልበት ቴክኖሎጂ ተግባራዊ መደረጉን ጠቁመዋል።

በቦረና አካባቢም በሰባት ትምህርት ቤቶች ላይ የተለያየ ሜትር ኪዩብ ውሃ ማጠራቀም የሚችሉ ሮቶዎች መዘጋጀታቸውን ጠቁመው፤ በተጨማሪም በጎንደር ከተማ በአራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ፕሮጀክቱ ተሞክሮ ውጤታማ መሆኑን ገልፀዋል። ፕሮጀክቱ የውሃ አቅርቦት ችግርን ለማቃለል እንደሚረዳም ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ በአሁኑ ሰዓትም ቴክኖሎጂውን በመጠቀም እና የውሃውን ጥራት በመጠበቅ ለተለያየ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል የማጣሪያ ቴክኖሎጂ ያለ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ ቀደም ኢንስቲትዩቱ ግቢ ውስጥ በመሞከር የፕሮጀክቱ አዋጭነት ተረጋግጦ ወደ ሥራ መግባቱን አብራርተዋል።


አቶ ታመነ ኃይሌ

«ለውጥን ለማምጣት መጀመሪያ መለወጥን ይጠይቃል» ያሉት ዳይሬክተሩ ተቋሙ የነበረበትን የአቅም ችግር ለመፍታት ከክልሎች፣ ከሚኒስቴር መስሪያቤቶች እንዲሁም ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን በተለይም ሴክተሩን ለሚቀላቀሉ ባለሙያዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ብቃት እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን ተናግረዋል። ለባለሙያዎች የሚሰጠውን ስልጠና በማስፋፋትም የሕዝቡን የውሃ ችግር በፍጥነት ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሴክተሩን ለሚቀላቀሉ ባለሙያዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚማሩት ባለፈ በእውቀት የተመራ ስልጠና እንደሚሰጥ ተናግረው፤ ከስልጠናው በኋላ ወደ ተግባር ተለውጧል የሚለውን እንደሚገመግሙ አብራርተዋል።

ዳይሬክተሩ እንደተናሩት፤ በኢትዮጵያ 20 ሚሊዮን ሕዝብ በቂ ውሃ አያገኝም፤ የውሃ እጥረት ሲያጋጥም ትምህርት የሚያቋርጥ ተማሪ ቁጥርም ይጨምራል። ይህንን ችግር ለመቅረፍም ፕሮጀክቱን በ120 አካባቢዎች ለመተግበር ታቅዷል።

የዝናብ ውሃን ከጣሪያ ላይ በመያዝ ለቤት ውስጥ አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስችለውን ቴክኖሎጂ ስኬታማ ለማድረግ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑንም አክለዋል።

ዘጠና በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ክፍል ሁልጊዜ ዝናብ የሚያገኝ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ቴክኖሎጂው ውሃውን ከጣሪያው ላይ ስቦ ለተወሰነ ጊዜ ከመሬት ውስጥ አከማችቶ፤ የውሃ እጥረት በሚኖር ጊዜ መጠቀም የሚያስችል በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል። ይህንንም አሠራር ለማስፋፋት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

# በ200 ሚሊዮን ብር በሴፍትኔት ፕሮግራም ለሰለጠኑ ዜጎች የመሥሪያ ቦታ ግንባታ ሊጀመር ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሴፍትኔት ፕሮግራም የሰለጠኑ ዜጎች የሚያጋጥማቸውን የመሥሪያ ቦታ ችግር ለመቅረፍ በመጪው ግንቦት ወር በ200 ሚሊዮን ብር ወጪ ግንባታ እንደሚጀመር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ ዕድልና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ኃላፊ አቶ ፍስሃ ጥበቡ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሴፍትኔት ፕሮግራም የሚሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎች ኑሯቸውን ሊያሻሽል የሚችል የሕይወት ክህሎት ስልጠና ወስደው ወደ ሥራ ለመግባት የሚያጋጥመውን የመስሪያ ቦታ ችግር ለመቅረፍ በትኩረት እየተሠራ ነው።

የሚያጋጥመውን የመስሪያ ቦታ ችግር ለመቅረፍ ከዓለም ባንክ በተገኘ 200 ሚሊዮን ብር በርካታ ተሳታፊ በሚገኙባቸው ልደታ፣ ጉለሌ፣ አዲስ ከተማ እና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ላይ ባለ አራት ወለል ሕንፃ ለመገንባት የጨረታ ሂደት ውስጥ የተገባ ሲሆን፤ ግንባታው በቀጣዩ ግንቦት ወር እንደሚጀመር አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ፍስሃ ገለጻ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በዝቅተኛ ወጪ ከሚያስገነባቸው ሕንፃዎች በወሰደው ተሞክሮ መሠረት፤ የሕንፃ ግንባታውን በአራት ወራት ለማጠናቀቅ እቅድ መያዙን አብራርተዋል።

የሕንፃ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለመሸጫ እና ማምረቻ አገልግሎት ከማዋሉም በተጨማሪ የመሥራት አቅም ለሌላቸው ማህበረሰቦች ለመኖሪያ ቤት እንደሚያገለግል አስታውቀዋል።

ባለፈው በጀት ዓመት በ93 ሚሊዮን ብር ወጪ በሁለት ክፍለ ከተሞች የ19 ሼዶች ግንባታ መከናወኑን ያስታወሱት ኃላፊው፤ ሼዶቹ ኤሌክትሪክና የውኃ መስመር እንደተገጠመላቸውና በመጀመሪያው የሴፍትኔት ምዕራፍ ተሳታፊ የነበሩ 169 ማህበረሰቦችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ አስረድተዋል።


አቶ ፍስሃ ጥበቡ

በሴፍትኔት መርሃ ግብሩ ላይ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ሙያተኞች ቤት ለቤት በመዞር ያላቸው የኑሮ ደረጃ፣ ቤታቸውና ያላቸው የቤት ውስጥ ዕቃዎች ተለክቶ ደረጃ ይወጣል። በወጣው ደረጃ መሠረት በየአካባቢው ስም ዝርዝር ተለጥፎ መልማይ ኮሚቴው የመመልመል ሥራ ይሠራል ሲሉም አስረድተዋል።

በሁለተኛው ምዕራፍ ተሳተፊ ከሚሆኑት 109 ሺህ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሰባት ሺህ ያለአግባብ የገቡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው ተብሎ ቅሬታ የቀረበ ሲሆን ጉዳዩ በድጋሚ ታይቶ መስተካከል ችሏል ብለዋል።

ያለአግባብ ገብተዋል የሚል ቅሬታ ያለው ማንኛውም ማኅበረሰብ ክፍል ወረዳ፣ ክፍለ ከተማ እና ከተማ አስተዳደሩ ላይ ማቅረብ እንደሚችሉ ጠቁመዋል። የሚቀርብ ቅሬታን ለመፍታት እና የሚቀርቡ ጥቆማዎችን አጥርቶ እርምጃ ለመውሰድ የሚመለከታቸው አካላት ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የሴፍትኔት መርሃ ግብር ከተጀመረ ጀምሮ በሁለት ምዕራፎች ከ530 ሺህ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን አስታውሰዋል።


አቶ እንግዳወርቅ ታደሰ

# የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን ምክንያታዊ ሊሆን ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በማኅበራዊ ሚዲያ የሚኖረን አጠቃቀም በምክንያታዊነት ላይ የተመረኮዘ ሊሆን እንደሚገባ በወሎ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ትምህርት ክፍል ኃላፊና መምህር አቶ እንግዳወርቅ ታደሰ ተናገሩ። የሃሰት መረጃዎች በአገር ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመቀነስ ተቋማት የተጣሩ መረጃዎችን በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ እንደሚገባቸውም ጠቁመዋል።

አቶ እንግዳወርቅ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማንም አካል አንድን መረጃ ስላወጣ ብቻ መቀበል አሊያም ተቀብሎ መተግበር ራስንም ሆነ አገርን ለከፋ ጉዳት እንደሚያጋልጥ መገንዘብ ይገባል።

በአገር ላይ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በሚዲያ ላይ የተሰማሩ አካላት ትክክለኛውን መረጃ በፍጥነት በመልቀቅ የማኅበራዊ ሚዲያን አጠቃቀም ለበጎ ተግባር እንዲሆን መሥራት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

አሁን ላይ ማህበራዊ ሚዲያ ፈጣን መረጃን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በተለይ ለተቋማት ትልቅ ገፀበረከትን አምጥቷል ያሉት አቶ እንግዳወርቅ፤ ተቋማት በእራሳቸው የማኅበራዊ ሚዲያ ገጽ ላይ ፈጣንና ትክክለኛ መረጃዎችን በየጊዜው በማቅረብ ሕዝብን ከሃሰተኛ መረጃዎች መጠበቅ እንደሚኖርባቸውም ተናግረዋል።

የመንግሥት ተቋማት ማኅበራዊ ሚዲያን ባህሪይ በመረዳት በሕግ ምስጢራዊ ከሆኑ መረጃዎች ውጪ ማንኛውንም መረጃዎች ሳይደበቁ በወቅቱ ማቅረባቸው ከሃሰተኛ መረጃዎች ጋር ተያይዞ የሚመጡ ጥፋቶችን ለመከላከል ይረዳል ሲሉ ገልጸዋል።

አቶ እንግዳወርቅ እንዳስታወቁት፤ መረጃዎች ከሕዝብ ሲደበቁና በቀላሉ ሳይገኙ ሲቀሩ ክፍተቱን በመጠቀም ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ሃሰተኛና ተዓማኒነቱን ያልጠበቀ መረጃ የመሠራጨት ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

መረጃዎች ከሕዝብ በተደበቁ ቁጥር ኅብረተሰቡ ተዓማኒነት የሌለውን መረጃ እውነት አድርጎ ስለሚቀበል በማኅበራዊ ሚዲያው ኃላፊነት የጎደለው አጠቃቀም የተነሳ ግጭት፣ የሕይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት ሊከሰት ይችላል ብለዋል።

በመሆኑም መንግሥት ማኅበራዊ ሚዲያን ላልተገባ ዓላማ የሚጠቀሙ ግለሰቦችን ሥርዓት ለማስያዝ ተጠያቂ የሚያደርገውን ሕግ ተግባራዊ ማድረግና የተዓማኒ መረጃዎችን ሥርጭት ማጠናከር ይገባዋል ሲሉም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ እንግዳወርቅ ገለፃ፤ አንድ ጉዳይ ሲከሰት የሚመለከተው አካል በሕዝብ ግንኙነቱ በኩል አሊያም በመደበኛ መገናኛ ብዙኃን በኩል ግልጽ መረጃን በወቅቱ ማቅረብ ቢቻል በማኅበራዊ ሚዲያ የሃሰት መረጃዎች አማካኝነት የሚደርሱ ችግሮችን መቀነስ ይቻላል።

ማኅበራዊ ሚዲያዎችን የሚጠቀም ማንኛውም ዜጋ ማንኛውንም መረጃ ሲያጋራ ኃላፊነት በተሰማው ስሜት መሆን አለበት ያሉት መምህሩ፤ ግጭትን ከሚቀሰቅሱ፣ የአገርን ጥቅም ከሚጎዱና ችግር ከሚፈጥሩ መረጃዎች በመራቅ እራስንና አገርን ከጥፋት ማዳን ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አቶ እንግዳወርቅ እንደገለጹት፤ የሚመለከታቸው ተቋማት ማኅበረሰቡ በማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ሃሰተኛ መረጃዎችን በፍጥነት ተቀብሎ ወደጥፋት እንዳያመራና በምክንያታዊነት ላይ የተመረኮዘ አጠቃቀምን እንዲያጎለብት ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ሊያስፋፉ ይገባል።

# ክልሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሁለት ሺህ 400 ሄክታር በላይ የበጋ መስኖ ስንዴ አልምቷል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በዘንድሮ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ባደረገው የበጋ መስኖ ስንዴ ከሁለት ሺህ 400 ሄክታር በላይ መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ በማልማት ማሳካቱን አስታወቀ። እስካሁን 74 ሄክታር ሰብል ተሰብስቧል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበከር ኻሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለማው የበጋ መስኖ ስንዴ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል። በመጀመሪያው ትግበራም ሁለት ሺህ 500 ሄክታር ላይ ለመዝራት ታስቦ ሁለት ሺህ 434 ሄክታሩን በዘር መሸፈን ተችሏል።

እስካሁን 74 ሄክታር ያህሉ ሰብል መታጨዱንና ስምንት ሺህ ኩንታል ምርት መገኘቱን የቢሮ ኃላፊው ጠቅሰዋል። ሰብሎቹ ተራ በተራ የሚደርሱ በመሆኑ ቀሪውን ለመሰብሰብ ዝግጅት እየተደረገ እንዳለም ገልጸዋል።

ሥራውን በአግባቡ ለማስኬድ በልማት ጣቢያዎች መሠረታዊ ሥልጠናዎች የመስኖ ልማት ግንባታዎች ተከናውነው ወደ ሥራ መገባቱን አስታውሰዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ በአካባቢው የተለመደ አልነበረም ያሉት ኃላፊው፤ የግንዛቤ ሥራዎች ተሠርተው ወደ ተግባራዊ ሥራ መገባቱንና በዚህም መልካም ተሞክሮ ማየት እንደተቻለ ተናግረዋል።

ከተዘጋጀው ውሃና መሬት አንጻር ሁለት ሺህ 500 ሄክታር ታቅዶ ሁለት ሺህ 434 ሄክታሩን በዘር መሸፈን ተችሏል ነው ያሉት። የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሕዝቡን የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ ለፋብሪካዎች በቂ የስንዴ ምርት ለማቅረብም ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ጠቅሰዋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው ሙከራ ውጤታማ መሆኑን የገለጹት አቶ ባበከር፤ ይህም ስንዴን በአካባቢያችን አምርተን መጠቀም እየቻልን ጠባቂ መሆን እንደሌለብን ትምህርት የሠጠ ነው ብለዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ማህበረሰቡ የተሻለ ልምድ እንዲኖረው በማድረግ፣ መቼ መዝራት እንደሚገባው፣ ለሰብሉ ምን እንደሚያስፈልገውና ምን ዓይነት ግብዓቶችን ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ በመለየት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ያስችላል ሲሉ ገልፀዋል።

ለቀጣይ የክረምት ስንዴ ልማትም ወሳኝ ተሞክሮ የተቀሰመበትና መሬት በአግባቡ ተዘጋጅቶ ከተዘራ ለውጥ የሚያመጣ ምርት ማግኘት እንደሚቻል የተገነዘብንበት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በክልሉ በ2015/16 ዓ.ም የመኸር እርሻ 50 ሺህ ሔክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ዝግጅት እየተደረገ እንዳለ ጠቁመው፤ ለዚህም ዘር፣ ኬሚካልና ሌሎች ግብዓቶች እየተዘጋጁ እንደሆነ አመላክተዋል።

ከመግዛት ይልቅ አምርቶ ራስን መቻል ትልቅ ፋይዳ ያለው ነው ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በክልሉ የበጋ መስኖ ስንዴ መጀመሩ ዜጎች የምግብ ዋስትናቸው እንዲረጋገጥ፣ አገሪቷ ምርቱን ለማስገባት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ በመቀነስ ረገድም ሚናው ቀላል እንዳልሆነ አስታውቀዋል።



አቶ ፈንታሁን ቸኮል

# በምሥራቅ ጎጃም ዞን ከ22 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰበሰበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2014/15 የምርት ዘመን 22 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት መሰብሰቡን የምሥራቅ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ።

የዞኑ ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ፈንታሁን ቸኮል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014/15 የምርት ዘመን 611 ሺህ 370 ሄክታር በዘር ለመሸፈን ታቅዶ 615 ሺህ ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል። በዚህም 22ነጥብ3 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተሰብስቧል ብለዋል።

ለዚህ ውጤት መገኘት ጥሩ የዝናብ ሁኔታ መኖር፣ የተገኘውን ማዳበሪያና ሌሎችንም ግብአቶች በአግባቡ መጠቀም መቻሉ፣ የተፈጠረውን ማዳበሪያ እጥረት ለመቅረፍ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ላይ አተኩሮ መሠራቱና በአርሶ አደሩ፣ በባለሙያውና በሌሎችም ባለድርሻ አካላት በኩል የተደረገው ርብርብ ትልቅ ሚና እንደነበረው ገልጸዋል።

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ፈንታሁን፤ በዘንድሮው ዓመትም እንደየ አካባቢው ነባራዊ ሁኔታ 49 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍን የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ተከናውኗል። ሥራው አንድ ጊዜ ተሠርቶ የሚያልቅ ስላልሆነ ለምርታማነት መጨመር የሚያበረክተውን ሚና በመረዳት አርሶ አደሮች ይህንን ሥራ አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በ2015/16 ምርት ዘመንም 23 ሚሊዮን የሚደርስ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጀመሩን ያመለከቱት አቶ ፈንታሁን፤ በዚህ የማሳ ዝግጅት፣ የማዳበሪያ አቅርቦት፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅትና የተዘጋጀውንም ወደ ማሳ የማውጣት ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል።

እንደ መምሪያ ኃላፊው ገለጻ፤ በክልል ደረጃ የፓኬጅ ክለሳ እየተከናወነ ነው። ይህን መነሻ በማድረግም የባለፈውን ዓመት ሥራና የእቅድ ግምገማን ያካተተ ምክክር ከባለሙያዎች፣ ከአርሶ አደሮችና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር ይደረጋል። በተጨማሪም የተከለሰውን ስልጠና መሠረት በማድረግ ለባለሙያዎችም ስልጠና እንደሚሰጥ ጠቁመዋል።

የማሳ ኩታገጠም ሥራ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ አመልክተው፤ በተለይ ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ የቢራ ገብስ፣ ማሽላና ቦሎቄ ሰብሎች ላይ የተሻለ ውጤት እንዲገኝ ለማስቻል የኩታ ገጠም ማሳ ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል ብለዋል።

ባለፈው ዓመት የነበረውን የማዳበሪያ እጥረትና የዋጋ ችግር ለመቅረፍ በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ አርሶ አደሮችም በባለሙያዎች ምክረ-ሀሳብ መሠረት የእርሻ ድግግሞሽ ላይ ማተኮር፣ ማዳበሪያ በወቅቱ መያዝና የተዘጋጁ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን በወቅቱ ወደ ማሣ የማውጣት ሥራ በመሥራት ለምርትና ምርታማነት መጨመር ሚናቸውን እንዲወጡ አሳስበዋል።



በባቢሌ ብሔራዊ ፓርክ ከሚገኙ ዝሆኖች

# የሕዝብ ሰፈራና ሕገወጥ አደን የብሔራዊ ፓርኮች ፈተና ሆኗል

## - በባቢሌ ብሔራዊ ፓርክ አስር ዝሆኖች ለህልፈት ተዳርገዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ሰፈራ፣ ሕገወጥ አደን እና ሕገወጥ የእንስሳት ዝውውር በብሔራዊ ፓርኮች ላይ ትልቅ ፈተና መሆኑን በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ባለስልጣን የብሔራዊ ፓርኮች አስተዳደር አስታወቀ።

በባለስልጣኑ የብሔራዊ ፓርኮች አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ አዳነ ጿጋዬ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በፓርኮች ውስጥና በፓርኮቹ ዙሪያ የሚደረግ የሕዝቦች ሰፈራ እንዲሁም ሕገ-ወጥ አደን ምክንያት ብዙ እንስሳት ለመጥፋትና ለሞት ይዳረጋሉ።

በሕገ-ወጥ ተግባራቱ የተነሳ በባቢሌ ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ባለፉት ዘጠኝ ወራት አስር ዝሆኖች ለህልፈት መዳጋቸውን የጠቀሱት ሥራ አስፈጻሚው፣ በአንጻሩም በዝሆኖች አማካኝነት በሰዎች ላይ በደረሰው ጥቃት አስር ሰዎች ለህልፈት መዳረጋቸውንም ገልጸዋል።

እንደ አዳነ (ዶ/ር) ገለጻ፣ በብሔራዊ ፓርኩ ላይ በርካታ ሰዎች ሰፍረዋል፤ ተቋማት እስከ መመስረት የተደረሰበት አግባብም አለ፤ የዛን ጥብቅ ስፍራ ሕጋዊነት በጣም የሚጋፉ ነገሮች እየተካሄዱ ያለበት ሁኔታ አለ፤ እንዲሁም በፓርኮች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ ሀብት ለመጠቀም በፓርኮቹ ላይ ብዙ ጉዳት ያደርሳሉ።

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በውስጡ ሰፈራዎች እንዲሁም ፓርኮቹን አቋርጠው የሚሄዱ የተለያዩ መንገዶች ስለነበሩ ካለፉት ጥቂት ዓመታት በፊት በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ የትምህርትና የባህል ድርጅት (UNESCO) ከዓለም ቅርስነት ለመሰረዝ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ እንደነበር አስታውሰዋል።

ችግሮቹን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተለያዩ ውይይቶችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል ያሉ ሲሆን በተለይ በመጥፋት ላይ ያሉትን እንስሳት በመለየት እንዲሁም ሕገ-ወጥ የእንስሳት ዝውውርን ለማስቀረት ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራን ነው ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው እየተመናመነ ከመጡ እንስሳት መካከል ዝሆን አንዱ እንደሆነ ያነሱት ኃፊው፤ በባቢሌ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኙትን ዝሆኖች ከመጥፋት ለመታደግ የሱማሌና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ፕሬዚዳንቶቹ በተገኙበት ሰፊ ውይይት ተደርጎ የተወሰኑ አባወራዎች ቦታውን እንዲለቁ ተደርጓል ብለዋል።

በፓርኮች ውስጥና በፓርኮች አካባቢ የሚገኙ ሕዝቦች ወደ ሌላ ቦታ ማስፈር እንዲሁም በፓርኮች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በፓርኩ ላይ ጫና የሚፈጥሩት ሀብትን ለመጠቀም በመሆኑ በፓርኩ ዙሪያ የሚኖሩ ማህበረሰቦች አማራጭ የገቢ ምንጭ የሚሆናቸውን የመፍጠር ሥራዎች ታቅደው እየተሠሩ መሆኑን የተናገሩት አዳነ (ዶ/ር)፤ ለማገዶ የሚጨፈጨፈውን ደን በማስቀረት ሌላ የኃይል አማራጮች ለኅብረተሰቡ በማሟላት በፓርኮቹ ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ አካላት ለእርሻ መሬት የሚያስፋፉ ሰዎች በኢኮቱሪዝምና ሌሎች የገቢ አማራጭ እንዲጠቀሙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በፓርኮቹ ዙሪያ ኢኮ-ቱሪዝም በሚስፋፉበት ላይ ይሠራል ሲሉም ጠቁመዋል።

በፓርኮቹ የሚስተዋለውን ሕገወጥ አደን ከመከላከል አንጻር ችግሩን ለመቆጣጠርና ለማስቀረት በፓርኮቹ ጠባቂዎች አማካይነት ከፍተኛ ጥበቃ እየተደረገ መሆኑን የገለጹት ዶክተር አዳነ፣ ሕገወጥ የእንስሳት ዝውውር ሌላኛው ከፍተኛ ተግዳሮት በመሆኑ ችግሩን ለመቀነስና ለመቆጣጠር የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ከጉምሩክና ከቦሌ አየር ማረፊያ ጋር በመተባበር በጋር እየሠራ ነው ብለዋል።

# «በኤሌክትሪክ መቆራረጥ ምክንያት ለአራት ዓመታት ተቸግረናል»

*- የዳዬ ከተማ ነዋሪዎች*

# «ችግሩ በሁለት ወራት ውስጥ ይፈታል»

*- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሲዳማ ሪጅን*

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ለአራት ዓመታት የዘለቀው የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ለበርካታ ችግሮች መዳረጋቸውን በሲዳማ ክልል የዳዬ ከተማ ነዋሪዎች ቅሬታ አቀረቡ። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሲዳማ ሪጅን በበኩሉ ችግሩን ለመቅረፍ እየሠራ መሆኑንና በሁለት ወራት ውስጥ መፍትሄ እንደሚሰጥ አስታውቋል።

የዳዬ ከተማ ነዋሪ አቶ የሱፍ አሊ ከአራት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ወደከተማዋ የሚለቀቀው የኤሌክትሪክ ኃይል በሰዓታት ልዩነት ይቆራረጣል። ለረጅም ሰዓትም ይጠፋል ሲል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየቱን ሰጥቷል።

በአንድ ቀን ውስጥ ብቻ በአማካኝ ከአራት ጊዜ በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ያጋጥማል ያለው አቶ የሱፍ፤ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ በከፍተኛ ምሬትና ችግር ውስጥ ገብቷል። ችግሩ ምግብ ለማብሰልም ሆነ በኤሌክትሪክ የሚከናወኑ ሥራዎችን ለመፈጸም አዳጋች ሆኗል ብሏል።

አሁን ላይ በሚቀርበው የተቆራረጠ ኃይል የተነሳ የከተማዋ ነዋሪ ኤሌክትሪክ እያገኘ ነው ማለት አይቻልም። ለረጅም ሰዓታት ጠፍቶ የሚመጣ በመሆኑ ችግሩን የሚመለከተው አካል መፍትሄ ሊሰጥበት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላኛው የዳዬ ከተማ ነዋሪ ወጣት መልካሙ ማርቆስ በበኩሉ፤ ወጥ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ አገልግሎት



ለማግኘት ተቸግረናል ብሏል።

የግል ንግድ የሚሰሩ ግለሰቦች ሥራቸውን ላለማቋረጥ ሲሉ ጄኔሬተር ገዝተው እየሠሩ ቢሆንም የቤንዚል መግዣ ገንዘብ ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ ሥራቸውን ለማቆም እየተገደዱ መሆኑን ወጣት መልካሙ አስታውቋል።

ፀጉር ቤቶች፣ ስቴሽነሪና ጎሚስታ እንዲሁም በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ የንግድ ቤቶች በኃይል መቆራረጡ የተነሳ ለኪሳራ መዳረጋቸውንና ችግሩ ከፍተኛ የሕዝብ ምሬት መፍጠሩን ተናግሯል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሲዳማ ሪጅን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አበበ ዕድሉ በበኩላቸው፤ በክልሉ ካሉ 15 የኤሌክትሪክ ማዕከላት ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ያለው የዳዬ ማዕከል ላይ መሆኑን ገልጸው፤ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግሩ በሁለት ወራት ውስጥ እንደሚፈታ ገልጸዋል።

የዳዬ ከተማ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ መሠረታዊ ችግር የኤሌክትሪክ መስመሩ ከይርጋለም ሰብስቴሽን ከወጣ በኋላ ዳዬ ከተማ እስከሚደርስ 110 ኪሎ ሜትር ርቀት ስለሚጓዝና በመሃል የሚያጋጥሙ መበላሸቶች ስለሚፈትኑት ነው ብለዋል።

ሌላኛው ምክንያት የሰብስቴሽን እጥረት በመፈጠሩ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከዳዬ ከተማ በተጨማሪ አለታ ወንዶ፣ ሀገረ ሰላምና ጭኮ ከተሞች እና ዙሪያቸው የሚገኙ 86 የገጠር ቀበሌዎች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት የሚያገኙት ከይርጋለም ሰብስቴሽን በመሆኑ ችግሩ መከሰቱን አስረድተዋል።

በ 86ቱ ቀበሌዎች የተዘረጋው የኤሌክትሪክ መስመር ዳዬ ከተማ እስኪደርስ በአንዱ ቀበሌ ላይ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሠራሽ ምክንያት ብልሽት ሲያጋጥመው የኃይል መቆራረጡ ይከሰታል ብለዋል።

የችግሩን አንገብጋቢነት በመረዳት ለዳዬ ከተማ እራሱን የቻለ የተለየ የኤሌክትሪክ መስመር በ100 ሚሊዮን ብር ወጪ እየተዘረጋ መሆኑን አቶ አበበ ገልጸዋል።

አቶ አበበ እንዳስታወቁት፤ የመስመር ዝርጋታው ሥራ በወሰን ማስከበር ምክንያት የተጓተተ ቢሆንም በሁለት ወራት ውስጥ የዳዬ ከተማ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግር ይፈታል።

ኅብረተሰቡ የመስመር ዝርጋታው ሥራ እስኪጠናቀቅ ድረስ በትዕግስት እንዲጠብቅ አቶ አበበ መልዕከታቸውን አስተላልፈዋል።

# በሳውዲ ዓረቢያ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሲጀመር በሳውዲ ዓረቢያ በእስርና በማቆያ ጣቢያዎች የሚገኙ 102ሺ ዜጎችን ለመመለስ ታቅዶ ሲሠራ ነበር።

ይሁን እንጂ ሕገወጥ ስደቱ ባለመቆሙና ወደ ኤምባሲ የሚመጡ ዜጎች ቁጥር በመጨመሩ የዛሬ ተመላሾችን ጨምሮ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የነበሩ ከ 131ሺ በላይ የሚሆኑ ዜጎችን መመለስ መቻሉን ጠቁመዋል።

ከሳውዲ ተመላሾች ባለፈ በተለያዩ አገራት ችግር ላይ የነበሩ ስምንት ሺ ዜጎችን የመመለስ ሥራ መሠራቱን ያስታወሱት አምባሳደር ብርቱካን፤ በዘመቻ የሚሠራው ሥራ ይጠናቀቅ እንጂ አሁንም ችግር ላይ ያሉ ዜጎችን የመመለሱ ተግባር አይቆምም ብለዋል።

የመንግሥትና የሕዝብም ፍላጎት ዜጎች በአገራቸው ሠርተው እንዲለወጡ መሆኑን ጠቅሰው፤ በውጭ አገራት የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ካሉም በሕጋዊ መንገድ መሄድ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ነሲቡ ያሲን በበኩላቸው፤ በሳውዲ ዓረቢያ በችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ለመመለስ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት 16 ተቋማትን ያካተተ ኮሚቴ ተቋቁሞ የግልና የጋራ እቅድ በማዘጋጀት ሲሰራ መቆየቱን አስታውሰዋል።

የመጀመሪያው ሥራ ዜጎችን ወደ አገራቸው መመለስ እንደነበር አስታውሰው፤ እስካሁን በነበረው ሂደት 350 የሚደርሱ በረራዎች ተደርገው ከ131ሺ በላይ ዜጎች ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ኮሚሽንም የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል አቋቁሞ ወደ አገር የሚመለሱ ዜጎችን ጊዜያዊ ማረፊያ ከማዘጋጀት ጀምሮ ከመነሻ እስከመዳረሻቸው አስፈላጊውን እገዛ ሲያደርግ መቆየቱን ገልጸው፤ ለአንድ ዓመት በዘለቀው ሥራም መንግሥት ከ493 ሚሊዮን ብር በላይ መድቦ ሲሰራ ነበር ሲሉ ጠቁመዋል።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ያደረጉትን የዓይነትና የገንዘብ እገዛ ጨምሮ ለዚህ ሥራ ከ542 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉንም አመላክተዋል።

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር እንዳሉት ደግሞ፤ አገልግሎቱ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ ለስደት ተመላሾች ከጤናና አገልግሎት ጀምሮ ወደቀያቸው መመለስን ያጠቃለለ ሥራ ሲሰራ እንደነበር አስታውሰው፤ የስነልቦና ችግሮችን የማከምና ከኅብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ የማድረግ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህም ባለፈ ዜጎች ስደትን አማራጭ ከማድረግ ይልቅ በአገራቸው ሥራ ተፈጥሮላቸው እንዲለወጡ የተለያዩ ተግባራት እየተከናውነ መሆኑንም አስታውሰው፤ ዜጎች ወደ ውጭ ሄደው መሥራት ካለባቸውም በሕጋዊ መንገድ ብቻ መሆን እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ዜጎችን ከመመለስ ባለፈ አስፈላጊው እገዛ ተደርጎላቸው በአገራቸው ሠርተው እንዲለወጡ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትብብር እየሠሩ መሆኑም ተጠቅሷል።

# በክልሉ በማዕድን ልማት ፈቃድ ከወሰዱ ከ250 በላይ አልሚዎች ውስጥ 20ዎቹ ብቻ ወደ ሥራ ገብተዋል

## - 45 የውጭ አገራት ሕገወጥ የወርቅ አዘዋዋሪዎችም በቁጥጥር ስር ውለዋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በማዕድን ልማት ለመሰማራት ፈቃድ ከወሰዱ ከ250 በላይ አልሚዎች መካከል ወደ ሥራ የገቡት 20 ብቻ እንደሆኑ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ በሕገ ወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውሩ የተገኙ 45 የውጭ አገራት ዜጎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ካሉት ማዕድናት የወርቅ ምርት ቀዳሚ ሲሆን የድንጋይ ከሰልና እብነበረድም በክልሉ ካሉ እምቅ የማዕድን ሀብቶች መካከል ተጠቃሽ ነው።

ክልሉ ካለው የማዕድን ሀብት አንጻር የሚፈለገውን ጥቅም እያገኘ እንዳልሆነ የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ መንግሥት ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ 35 በመቶ ማበረታቻ ቢሰጥም በሚፈለገው ልክ አልገባም ብለዋል። በዚህ አመት የተገኘው የወርቅ ገቢ ከባለፈው አመት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው፤ ወርቅ አምርተው በቀጥታ ባንክ እንደሚያስገቡ ውል ወስደው ወደ ሥራ የገቡት ከ200 በላይ የሚሆኑ ፈቃድ የተሰጣቸው የወርቅ አዘዋዋሪዎች አሉ ሲሉም አክለዋል፤ ከእነዚህ ውስጥ ከ50 በላይ የሚሆኑት ወርቅ ለማስገባት ባንክ ቤት ገብተው እንደማያውቁ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ካሚል ገለጻ፤ በክለልሉ በወርቅ ማምረትና አዘዋዋሪነት ፈቃድ ከተሰጣቸው ውስጥ የትኞቹ ወደ ባንክ አስገቡ፣ የትኞቹስ አላስገቡም የሚል የልየታ ሥራ በመሥራት ወደ ባንክ ባላስገቡት አካላት በፈቃድ አስተዳደር መመሪያ ደንቡ መሠረት እርምጃ መውሰድ ተጀምሯል። ሥራ ውስጥ ያልገቡትንም በቀጣይ ወደ ሥራ ለማስገባት ቢሮው ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመቀናጀት እየተሠራ ነው።

ሕገ ወጥ የወርቅ ዝውውሩ በጌጥ መልክና ሌሎች ስውር ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከናወን ነው ያሉት አቶ ካሚል፤ ሕገ ወጥ ዝውውር በመደረጉ በወርቅ ምርት ላይ የተገኘው ገቢ ዝቅተኛ ሆኗል። የቁጥጥር ሥርዓቱም በልኩ አልነበረም። ስለዚህ አሁን ላይ በወርቅ ምርት ላይ የገቡ አልሚዎችን ቁጥጥር ማጠናከር አንዱ እርምጃ ነው። በተጨማሪም በተለያዩ ኬላዎች፣ ከክልሉ ፖሊስ፣ ልዩ ኃይል፤ ፌዴራል ፖሊስ ጋር በመቀናጀት በሕገወጥ መንገድ የሚካሄደው ሕገ ወጥ የወርቅ ዝውውር መቆጣጠር ላይ ቀጣይ ትኩረት የተሰጠው እርምጃ መሆኑን ተናግረዋል።

በክልሉ አሁን ላይ አንጻራዊ ሰላም እንዳለ የገለጹት ቢሮ ኃላፊው፤ ፈተናው በወርቅ አዘዋዋሪዎችና አምራቾች ላይ ወደ ባንክ ከሚያስገቡ ይልቅ በሕገ ወጥ መንገድ የተሻለ ገቢ ስለሚያገኙ ለቁጥጥር አንዱ ፈታኝ የሆነ ጉዳይ ነው። ሕገ ወጥ ነጋዴዎችን ለማግኘት መቸገር፣ አየር መንገድም የፍተሻ ማሽን እንዳይለየው የሚያስችል ኬሚካል እየቀቡ የሚያዘዋውሩ ስላሉና ወርቅ በባህሪው ትንሽ ስለሆነ ለመቆጣጠር አዳጋች አድርጎታል ብለዋል።

አቶ ካሚል 45 የውጭ ዜጎች በሕገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋውሩ በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው በፌዴራል እና በክልሉ መንግሥት ምርመራ ቡድን እየታየ ነው። ሌሎች 5 ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤትና በአስተዳደራዊ መንገድ ታይቷል ነው ያሉት።

የእምነበረድና የድንጋይ ከሰል ምርት ፍቃድ ከወሰዱ ከ250 በላይ አልሚዎች 20 ያክሉ ብቻ ወደ ሥራ መግባታቸውን የጠቆሙት ቢሮ ኃላፊው፤ ሌሎች ሥራ ውስጥ ለመግባት ፍላጎት ቢኖራቸውም መግባት አልቻሉም። ሥራ ውስጥ መግባት ያልቻሉበት ዋና ምክንያት በፀጥታ ስጋት ሲሆን ይህም ከክልሉ ውጪ ባሉ መንገዶች ላይ የሚፈጠር ነው። በክልሉ ግን ጠረፋማ አካባቢዎች ካልሆነ በስተቀር አብዛኛው አካባቢ ላይ ምንም ዓይነት የፀጥታ ችግር ባለመኖሩ ማሠራት የሚችል ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል።

ባለፉት ወራት በማዕድን ዘርፍ በልዩ አነስተኛ የወርቅ ማህበራት፣ በእምነበረድና በድንጋይ ከሰል ሥራ ለ2 ሺህ 250 ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ1ሺህ 765 ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ገልጸዋል።

# የኢትዮጵያና ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዘመን ጀምሮ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አላቸው። ይህን ግንኙነት ለማጠናከር በሁለቱም ፓርላማዎች በኩል ፍላጎት አለ ሲሉ ተናግረዋል።

ምክር ቤቱ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ ሥራዎች የሚያጠናክሩ የተለያዩ ክንውኖች እያደረገ ይገኛል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከዋና ተግባራቱ መካከል የአስፈጻሚ አካላትን መቆጣጠርና መከታተል፣ የሕዝብን ውክልና ማረጋገጥ እንዲሁም ፓርላሜንታሪ ዲፕሎማሲን ማከናወን ነው ብለዋል።

በዚህ ፓርላሜንታሪ ዲፕሎማሲ ዘርፍ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ፓርላማ ጉባኤዎች ላይ ተሳትፎና ምክክር አድርገናል። በቅርቡም የአፍሪካና ሩሲያ ፓርላማ ጉባኤ ላይ ተሳትፈን ጥሩ ሥራዎችን አከናውነናል ሲሉ ዶክተር ዲማ አስረድተዋል።

በተጨማሪ የአፍሪካ ካረቢያን ፓሲፊክና የአውሮፓ የጋራ ፓርላማ፣ የፓን አፍሪካ ፓርላማ ጉባኤዎች ላይ መልካም እንቅስቃሴዎች በፓርላማ ደረጃ እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ከተለያዩ አገራት ጋር የፓርላማ ቡድን አባላትን በማነጋገር ለአገራችን የዲፕሎማሲ ዘርፍ ውጤታማነት የበኩላችንን ለመወጣት ጥረት እያደረግልን ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህ አግባብ ከዩናይትድ ኪንግደም የፓርላማ አባላት ጋር የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ በሚያስተዋውቅና የአገራቱን ፓርላማ ግንኙነት በሚጠናከሩባቸው ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ውይይት አድርገናል ብለዋል።

ተመሳሳይ ውይይቶች የኢትዮጵያንና የዩናይትድ ኪንግደምን ወዳጅነት ለማጠናከር የሚረዳ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዲማ፤ ቋሚ ኮሚቴውም በዲፕሎማሲው መስክ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማ አባላት ልዑክን የመሩት ሮቢን ሚሌር በበኩላቸው፤ በዩናይትድ ኪንግደምና በኢትዮጵያ ፓርላማ መካከል በትብብር መሥራት ስለሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ምክክር መደረጉን ገልጸዋል።

የሁለቱ ፓርላማዎችን ግንኙነት ላቅ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግ ፍላጎት አለ፤ ለዚህም የሚረዳ ምክክር በኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መከናወኑ አንድ ርምጃ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያና የዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማ አፈ-ጉባኤዎች በቀጣይ ተገናኝተው ግንኙነቱን የሚያሳድጉበትን መንገድ ለማመቻቸት የሚረዳ ውይይት ነበረን፤ ውይይታችንም ውጤታማ ነው ብለዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ለዩናይትድ ኪንግደም ፓርላማ አባላት ስለኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታዎችና ስለሁለቱ አገራት ግንኙነት ገለጻ አድርገዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሕዝቦችን አብሮነት በሚያጎለብቱ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ መስራት ከሁሉም ይጠበቃል

ለሕብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያ የሕብራዊት ገጿ የሆኑት ሕዝቦቿ በአንድም በሌላ መልኩ የሚያስተሳስሯቸው አያሌ ጉዳዮች አሏቸው:: የቋንቋ፣ የባህል፣ የእምነት፣ የአመለካከትና ሌሎችም የበዙ ማንነቶች ያላቸውን ያህል፤ በቋንቋ ያልተገደበ፣ በሃይማኖት ያልተከለለ፣ በባህል ያልተጋረደ፣ በነገድ ያልታጠረ፣ በጥቅሉ የበዙ ልዩነቶቹ አጥር ያልሰሩበት፣ ወሰን ያላበጁበት የእርስ በእርስ መስተጋብርና የጠነከረ አንድነትን የፈጠሩ ሕዝቦች ናቸው::

ኢትዮጵያዊነት በአማራነት፣ በኦሮሞነት፣ በትግሬነት፣ በሶማሌነት፣ በአፋርነት፣ በወላይታነት፣... ተለክቶ የሚቀርብ ሳይሆን፤ አማራው ከትግሬው፣ ኦሮሞው ከሶማሌው፣ አፋሩ ከአማራው፣ ወላይታው ከሲዳማው፣ በሕብር ተደምሮ በአንድነት የሚደምቅበት ሕያው የማንነት ሰገነት ነው:: በዚህ ሰገነት ላይ የሚገለጡ ኢትዮጵያውያንም ተናጥላዊ ማንነታቸው ሳይሆን ሕብረ ብሔራዊ መጠሪያቸው፤ የባህል፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖትና ሌሎችም ወሰን አላባ የጋራ ማንነቶቻቸው ገዝፎ የሚስተዋልባቸው ናቸው::

"ከሚያለያዩን ይልቅ አንድ የሚያደርጉን እልፍ ጉዳዮች አሉን" እንዲል ብሂሉ፤ እኛ ኢትዮጵያውያንም ዛሬ ላይ ሊያለያዩን እና ላያግባቡን የሚችሉ መስለው ገዝፈው የሚታዩን አያሌ ጉዳዮች እንዳሉ ቢታሰብም፤ እውነቱ ግን በትናንት ሂደት፣ በዛሬ ኑረትና በነገ ተስፋችን ውስጥ ገናን የሆኑ አብሮነቶች፣ ሃያል የሆኑ መስተጋብሮች፣ ወሰን አልባ የጋራ ተስፋዎች ባለቤቶች መሆናችን ነው::

ለዚህም ነው ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ ቡድኖች የሴራ መስመር ሳይፈቱ፤ በጥቅመኞች የከፋፋይነት አጀንዳ ሳይጠለፉና እጅ ሳይሰጡ፤ በለውጥ ለበስ ነውጥ አራማጆች ነፍጥ እንዲማዘዙ ሲደረግ እንኳን አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ቂምና ቁርሾን ከመቋጠር ይልቅ የአብሮነታቸው ገጽ በዝቶ ሲገለጽ የሚስተዋለው:: ለዚህ ደግሞ ለጠብና ቁርሿቸው ይቅርታና እርቅን ያበጁ፤ ለዘላቂ ሰላማና አብሮነታቸው ካሳና የላቀ መተሳሰርን ያሰናዱ ሕዝቦች መሆናቸውን በተግባር እየገለጡ ከትናንት ዛሬ ደርሰዋል፤ ከዛሬ ተሻግረው ነገን በአብሮነት ለመዝለቅ ቃልኪዳን አስረዋል::

ይሁን እንጂ ይሄ የሕዝቦች አብሮነት እና ጠንካራ ትስርስ በየዘመናቱ በተለያዩ ምክንያቶች መፈተኑ አልቀረም:: ለምሳሌ፣ በቅርቡ የተካሄደው በሰሜኑ ጦርነት በተለይ የትግራይ፣ አማራ እና አፋር ክልሎች ላይ በትሩን ያሳረፈ እንደመሆኑ፤ በእነዚህ አከባቢ ያሉ ሕዝቦች ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ በማህበራዊ እና ሕዝባዊ መስተጋብሮች ላይ ማሳረፉ አይቀሬ ነው:: ይህ ደግሞ በማህበራዊ ሚዲያው እና መለያየትን ሰባኪ በሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች እሳት ቆስቋሽነት ሲታገዝ በህዝቦች መካከል መለያየትና ጸብን የመፍጠር አቅሙ ከፍ ያለ ነው::

ነገር ግን የእነዚህ ሕዝቦች አብሮነት፣ በደምና በአጥንት ተሳስሮ የተገነባ ማንነት በምንም መልኩ ሊላላም ሆነ ሊበጠስ እንደማይችል በጦርነቱ ወቅት ጭምር ታይቷል:: ምክንያቱም ከትግራይ ክልል ተፈናቅለው ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች የተሰደዱ ሕዝቦችን የአማራ እና አፋር ክልል ሕዝቦች በወንድማዊ ፍቅር ተቀብለው የችግር ጊዜን እንዲሻገሩ አድርገዋል:: በትግራይ ክልል ያሉ ሕዝቦች በወቅቱ በቦታው የነበሩ የአማራ፣ የአፋር፣ የኦሮሞና ሌላም ብሔር ተወላጆችን ችግር እንዳይደርስባቸው ከልለው አቆይተዋል፤ ነፍሰጡር አዋልደው ለእናትነት ክብር አብቅተዋል::

እነዚህና መሰል የህዝቦች እውነተኛ ገጽ የሆኑ ተግባራት "ውቅያኖስን በጭልፋ "እንዲሉት አይነት ለማሳያነት ተቀንጭበው ቀረቡ እንጂ፤ ኢትዮጵያውያን ለአብሮነታቸው መጽናት መሰረት የሆኗቸው አያሌ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል::ምክንያቱም፣ ኢትዮጵያውያን የሚያተርፉት በመለያየት ሳይሆን በአብሮነት መሆኑን የተገነዘቡ፤ መበልጸጋቸው በሕብር ሲሰሩ እንጂ ሲናጠቁ አለመሆኑን፤ ወደ ከፍታና ልዕልናቸው የሚደርሱት ፍቅርና አብሮነታቸውን አጽንተው ሲዘልቁ መሆኑን ቀድመው በመረዳት እየተጓዙ ያሉ ሕዝቦች ናቸው::

እዚህ ጋ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ይሄን የሕዝቦች አብሮነት፣ አንድነትና በጋራ ሆኖ ስለ ነገ የጋራ ተስፋቸው በሕብር ቆመው መራመዳቸው ያልተዋጠላቸው በርካታ አካላት ይሄንን የአብሮነትና አንድነት መሰረት ለመናድ የማይቆፍሩት ጉድጓድ አለመኖሩን ነው:: ዛሬም በአማራ እና በትግራይ፣ በአማራ እና በኦሮሞ፣ በኦሮሞ እና በሲዳማ፣ በኦሮሞ እና በሶማሌ፣ በሶማሌ እና በአፋር፣... ሕዝቦች መካከል ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፤ ከይቅርታ ይልቅ ቂምን፤ ከመተሳሰብና በጋራ ከመቆም ይልቅ መነጣጠልና መከፋፋትን... እየሰበኩ ጦር ለማማዘዝ የሚሰሩ የጥፋት ቡድኖች ማህበራዊ ሚዲያውን ሞልተው የጥላቻና የመከፋፈል መርዛቸውን እያሰራጩ ይገኛሉ::

ሕዝቡ ሰላም ሲል፣ ጦርነት መስበክን፤ ሕዝቡ ፍቅር ሲል፣ ለቂም ማነሳሳትን፤ ሕዝቡ አብሮነት ሲል፣ በሃሰት ትርክት ታግዞ መለያየትን፤ ሕዝቡ በይቅርታ መሻገርን ምርጫው ሲያደርግ፣ የቂምና ቁርሾ ስብከትን በተናበበና በተቀናጀ መልኩ ማስተጋባቱን የሕልውናቸው መሰረት አድርገው ይዘውታል::

የእነዚህ ኃይሎች ግብ ዛሬ ላይ ከቅዠት የዘለለ ሊሆን ባይችልም፤ ኢትዮጵያውያንን መለያየት እና በተለያየ ማንነት ውስጥ የተዳከሙች (ከተቻለም የተበታተነች) እና በቀላሉ የምትዘወር ኢትዮጵያን መፍጠር ነው:: ይህ የሚሆነው የኢትዮጵያዊነትን ገመድ መበጠስ፤ የኢትዮጵያውያንን አብሮነት መናድ ሲቻል እንደሆነም ተረድተው እየሰሩ ነው::

የነዚህን ሀይሎች ለመቀልበስ፣ ኢትዮጵያውያን የቀደመውን የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን አጠንክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፤ የሴረኞች የሴራ መረብ እርሱ ጋር ሳይደርስ እንዲበተን፤ ኢትዮጵያ እንደ አገር፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ በሕብር በደመቀውና በጸናው ማንነታቸው እንዲዘልቁ፤ የሕዝቦችን አብሮነት በሚያጎለብቱ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ መስራት ከሁሉም ይጠበቃል::


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ወደ መልካም እሴቶቻችን በመመለስ ለአገር እንትረፍ

ክብረ ነገስት

አሁን ላይ ተደጋግሞ ከምንሰማቸው ንግግሮች መካከል ‹‹ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ›› የሚለውን ሃሳብ ነው:: አባቶቻችን ‹‹የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› ማለታቸው ለዚሁ ነው:: ለራሳችን ችግር ሁነኛ የመፍትሔ ራሳችን ነን:: እኛ ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም የራሳችንን ችግሮች በራሳችን ተደጋግፈን የምንፈታ ቢሆንም በአፅዋማት ወቅቶች ግን የሚደረጉ መደጋገፎች በአይነታቸው የተለዩ ናቸው::

በጾም ወቅቶች እርስ በርስ ከመደጋገፍ አንጻር እኛ ኢትዮጵያውያን ስንተግብረው የኖርነው ሁነኛ መታወቂያችን ነው:: ተደጋግፈን ዓመታትን ብሎም ዘመናትን ኖረናል፤ ተሻግረናልም:: ዘመነኛ የሆነው የዘመኑ ትውልድ አባቶቹ ያቆዩትን የራስን ችግር በራስ የመፍታት እና የመተባባር እሴቶችን ከመተግበር አንጻር የተወሰኑ ዙሪያ ክፍተቶች ቢኖሩበትም አሁንም ከአባቶቹ የተማራቸውን አገር በቀል እውቀቶች እና እሴቶች እያስቀጠለ ይገኛል::

በቀደመው ጊዜ የነበሩን እሴቶቻችን እና አገር በቀል እውቀቶቻችን ለመሸርሸራቸው ምክንያት ለማወቅ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም በእኔ ግምት ግን አንዱ እና ዋነኛው ምክንያት የአሁኑ ትውልድ አብዛኛዎቹን የአባቶችን የቀደመ ገድሎች የሚሰማው በተጨባጭ ሳይሆን በአፈ ታሪክ እና በተረትተረት ብቻ መሆኑ ይመስለኛል::

ብናውቅበት እንደ አገር ለችግሮቻችን መፍትሔ የምንሰጥባቸው የራሳችን መገለጫ የሆኑ በርካታ አማራጮች ያሉን ሕዝቦች ነበርን:: ከእነዚህ አማራጮች ውስጥ በሕይወት ኖረንባቸው ጭምር ለሌሎች ምሳሌ ሆነናል:: ለዚህም በአፅዋማቶቻችን ወቅት የምናደርገውን አንዳንዱን ተግባራት በቂ ማሳያዎች ናቸው:: እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ በጥበብ ተለክተው በጥበብ የተቆረጡ ናቸው::

የበርካታ የምዕራባውያን የስልጣኔ መነሻዎች የእኛ አገር በቀል እውቀቶች እና እሴቶች ሆነው ሳለ የአሁኑ ትውልድ ይህን አምኖ ለመቀበል ሲቸገር ይታያል:: በቀደመው ጊዜ፣ በተለይ በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ለራሳችን ችግር መፍትሔው ራሳችን ከመሆን አልፈን ለሌላው ዓለም ሁሉ ስንተርፍ ስለ መኖራችን ከበቂ በላይ ማስረጃዎቹ ቢኖሩንም ነጮች ስላልነገሩን ብቻ አምነን መቀበል ግን አንፈልግም:: ይህ ትክክል አይደለም! ሊታረም ይገባዋል::

በነገራችን ላይ ባህላዊ አልባሳቶቻችን፣አመጋገባችን፣ የባህላዊ ህክምና አሰጣጣችን፤ ግጭት አወጋገድ ዘዴአችን እና ሌሎች ተዝቀው የማያልቁ አገር በቀል እሴቶቻችን እኛ ኢትዮጵያውያን ትላንት ማን እንደነበርን ለዓለም ህዝብ በተግባር ተገልጠን የታየንበት ነው::

ያኔ ለሚያስፈልጉን ጉዳዮች ሁሉ መፍትሔዎቹ ራሳችን ሆነን ችግሮቻችንን አስወግደናቸዋል:: ህመሞቻችንን አክመናቸዋል:: ተግባራቸውን ተዋደንባቸዋል፤ አለህልኝ፤ አለሽልኝ ተባብለንባቸዋል::

እኛ የብዙ ችግሮች መፍቻ ቁልፍ ባለቤቶች ነበርን:: በአርምሞ እንጂ በንግግር፣ በተግባር እንጂ በዝርዝር ሊገልጹን የማንቻል ብዙ ነገር ያለን:: ቅይጥ ያሉ ሰበዞች የሰፏት ሞሶብ፣ ዓይነት ብዙ ድርና ማጎች የሸመኗት ጋቢ ነን:: ልዩ ልዩ ቅመሞች የሠሯት ወጥ፣ ብዙ ገባሮች የፈጠሯት ዓባይም እንደኛ ያለ ማንም የለም::

ብዙ ትውልዶች የከመሯት ተራራ፣ ከአራቱ አቅጣጫ ተሰብስቦ በአንድ ወፍጮ የተፈጨች እህል ነን:: በአንድነታችን የምንደምቅ፤ በልዩነታችን ህብረብሔራዊነትን የምናጸባርቅም እኛ ብቻ ነን:: ውበታችን በልዩነት ውስጥ ሳይሆን በአንድነት ውስጥ የሚያበራልን ነው:: ለዚህ አንድ አብነት ብናነሳ የጾም ወቅት በሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ ሲጾም ከምግብ መከልከል ብቻ አይደለም፤ ክፉ ከመናገርና ከመተግበር የሚከለክል ነው::

ጾም ከሚያስገኘው መንፈሳዊ በረከት በተጨማሪ ለአካላዊ ጤንነት የሚሰጠው ጠቀሜታ አለው። የመጀመሪያው ሰውነታችን መቼ ምን ማግኘት እንዳለበት የሚነግረን ነው:: ምን መብላት እንዳለብን ትኩረት እንድናደርግም ያስችለናል። ሁለተኛው ክብደታችንን መቆጣጠርና፣ የካሎሪ መጠን መወሰን ስለሚያስችል ነው። ይሁንና ዋና ትኩረታችን የጾምን ጥቅም ማብራራት ሳይሆን ችግሮችን አብሮ መፍታት በመሆኑ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ:: ይህም የጾም ወቅት መልካም ተግባር ሲሆን፤ አንዱ ደግሞ ምጽዋት በሙስሊሙ አጠራር ደግሞ ሰደቃ ነው:: ይህንን በክርስትናው ስናነሳው ዓብይ ጾም ላይ ነንና ሳምንታቱ የተለየ ትርጓሜ ተሰጥቷቸው ለተቸገሩ ሁሉም ሰው ይደርስባቸዋል:: የመልካም ሥራ ማድረጊያ ቀናት ተደርገውም ይወሰዳሉ::

መመጽወት አንዱ የጾም አካል ነውና እንደግዴታም ተደርጎ ይወሰዳል:: ስለዚህም በክርስትናው ወራቱ በሙሉ የመስጠት ጊዜ ናቸው:: ወደ እስልምናው ስንገባም ይኸው ጉዳይ ይቀጥላል:: አሁን የገባው የረመዳን ጾም ደግሞ ለዚህ ምስክራችን ይሆናል:: ይህ ወቅት ለእስልምና እምነት ተከታዮች በረከት የሚታፈስበት ነው:: ምክንያቱም በሰደቃ የነፍስ ስንቅን ይሰንቃሉ::

ሰደቃ (ምጽዋት) የግዴታ አይደለም በበጎ ፈቃድ የሚተገበር መልካም ሥራ ነው:: የግዴታ ሲሆን በዘካ መልኩ ያደርጉታል:: ይህ ማለት ዘካ የኛ ሳይሆን የድሆች ገንዘብ ነው፤ የሀብታሞች የኑሮ መሰረት ደግሞ ድሆች ናቸው:: ስለዚህም የእነርሱን ገንዘብ መከልከል አይቻልም:: አንድ ሰው ይህንን ካደረገ ድርቅ ይመጣል፣ ዝናብ ይቀራል፣ አገር ይራባል ተብሎ ይታመናል:: በመሆኑም ለአገር፣ ለራስ በረከት ለማምጣት ሲባል ይህንን የማያወጣ ሰው አይኖርም:: ወደ ሌላኛውና በጎ ፈቃዱ ስንገባ ደግሞ መልካም ንግግር፣ ሰዎችን በሀሳብም፣ በገንዘብም ሆነ በጉልበት ማገዝ፣ የተጣሉትን ማስታረቅ የሚሉት ይካተታሉ::

የተራበን ሰው ያበላውን አላህ ነገ ከጀነት ፍሬ ያበላዋል:: የተጠማውን ያጠጣዋል:: የታረዘን ያለበሰውን ከጀነት ልብስ ያለብሰዋል:: የሰደቃ ጥቅሙ በዚህም ሆነ በመጨረሻው ዓለም ሰፊ ነው:: ለሰጭው ውስጣዊ እርካታ ሲሆን ለተቀባዩም ትልቅ ጥቅም አለው ተብሎ ይታመናልና በጾም ወቅት የሚተገበር ነው::

ሰደቃ መከራን ትመልሳለች፣ ችግርን ታስወግዳለች፣ እሳትን ታጠፋለች:: ሰደቃ ለብዙ ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ችግሮቻችንና በሽታዎቻችን የታዘዘች ልዩና ዓይነተኛ መድኃኒት ናት:: የደረቀ ቀልባችን ይለስልስ ዘንድ ወላጅ አጥ የሆኑ ልጆችን ራስ እናብስ:: በሽተኞቻችንን ሰደቃ መስጠት በማብዛት እናክም:: የምጽዋት ትንሽ የለውም:: ምክንያቱም የአንድን ሰው ሰደቃ ያሳድጋትና ትልቅ ምንዳ ይሰጠዋል ተብሎም በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ ይታመናል:: ይህ ታዲያ ከምን ይታደጋል ከተባለ መልሱ ቀላል ነው:: እንደሚታወቀው ይህ ወቅት ሁሉም በችግር ላይ ችግር የተደራረበበት ነው::

ችግር በተደቀነበት ጊዜ ሃይማኖት ተገን ሆኖ፤ መፍትሔ አመላካቾች ችግሮችን የሚፈታባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያ ናት:: ታዲያ ለምን የአገራችንን ችግር በአገራችን መፍትሔ ማስቀጠል አቃተን ከተባለ መልሱ ቀላል ነው:: እኛነታችንን ያለመቀበላችን ሁኔታ ይመስለኛል::

ሰው መጀመሪያ በራሱ እምነት ካለው መጀመሪያ ችግሩን ለመፍታት የሚነሳው ከቤቱ ነው:: ማንም ችግሩን ሳይሰማበትም ነገሮችን አልጋ በአልጋ ማድረግ ይቻላል:: ሆኖም በራሱ የማይተማመን ከሆነ ግን ገና ያልተተገበረውን ሀሳቡን ሳይቀር ይበትነውና ለሌሎች መወጣጫ ይሆናል:: ሀሳቡ ተቀምቶበትም ባዶ እጁን አጨብጭቦ ይቀራል:: እንደ አገር እየሆነም ያለው ይህ ይመስለኛል:: የእኛ የሆነ ብዙ ነገር አለን:: ግን የሌሎች አገራት ማንነት ይናፍቀናል:: ሳንሰራና ያለንን ሳንጠቀምበት በዓይናችን መስረቅ ብቻ ላይ ተጠምደናል:: እርሱ ብቻ አይደለም ለአገሩ የሚሰራ ስናይም ያመናል:: ለመጣል የማንቆፍረው ድንጋይ አይኖርም::

ባህል አክባሪው፤ ሃይማኖቱን ጠባቂው፤ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ለማልማት የሚጥረውን ከዚህ ውጣልኝ፤ እዚህ ማልማትና መኖር አትችልም ማለት ከጀመርንም ሰነባብተናል:: ይህ ደግሞ « .... አሳይተህ ጭብጦውን ቀማው» ለሚሉ አገራት መንገድ ጠራጊ ነው:: እኛን አባልተው እነርሱ የሚጠቀሙበትን ስርዓት ይዘረጋሉ:: ከየአበባው ተቀስማ በአንድ ቀፎ የተሠራችውን ማር አገራችንን እኛ ሳንጠቀምባት እነርሱ መጠው መጠው ይጨርሷታል:: የሚያስተርፉልን ነገር እንኳን አይኖርም:: ምክንያቱም በሌሎች አገራት ላይ አድርገውት አይተናል::

ስለዚህም ከየእህሉ ተዋጥቶ በአንድ ማድጋ በመልካም ሴት የተጠመቀችውን ጠላ፣ ከየእንጨቱ ተለቅማ በአንድ ጽንሐ የታጠነችውን መልካም ሽቱ ያላት ዕጣን የሆነችውን አገራችንን ላለማስነጠቅ ያለንን አይተን በአንድነታችን ችግሮቻችንን ልንፈታ ይገባል:: ቁልፋችን ብዙውን ነገር የሚፈታ ነውና ከመዛጉና ከመጣሉ በፊት እንጠቀምበት በማለት ሀሳቤ እቋጫለሁ:: ሰላም!!

# ነፃ ሀሳብ

# የህዳሴ ግድባችን፤ ከመጋቢት 24/2003 ዓ.ም እስከ ዛሬ

ገርማ መንግሥቴ

**አጠቃሳይ መረጃ**

- ግድቡ የሚገኝበት ቦታ - ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ጉባ ወረዳ
- የግድቡን ግንባታ የሚያከናውነው ሥራ ተቋራጭ - የጣሊያኑ ሳሊኒ ኢምፐሬጂሎ
- የሚያመነጨው የሃይል መጠን - 6 ሺህ 450 ሜጋ ዋት
- ለመገንባት የሚያስፈልገው ገንዘብ መጠን - 80 ቢሊየን ብር (የመሰረት ድንጋዩ ሲጣል፣ ከ4 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ)
- የሃይል ማመንጫ ዩኒቶች ብዛት - 13
- እያንዳንዱ ዩኒት የሚያመነጨው የሃይል መጠን - 6ሺህ 450 ሜጋ ዋት
- የዋናው ግድብ ከፍታ - 145 ሜትር
- የዋናው ግድብ ርዝመት - 1 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር
- የዋናው ግድብ ውፍረት - የግድቡ ግርጌ 130 ሜትር ሲሆን የግድቡ ጫፍ ወይም የላይኛው ክፍል 11 ሜትር፤
- ግድቡ የሚይዘው የውሃ መጠን - 74 ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር
- ግድቡ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት - 1 ሺህ 680 ስኩዌር ኪሎ ሜትር
- ሲጠናቀቅ ውሃ የሚተኛበት መሬት ርዝመት 246 ኪሎ ሜትር
- ግንባታው አሁን ላይ 84 በመቶ ደርሷል።

(ምንጭ፡- የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት)

ዓመታዊ አማካይ የውሃ ፍሰት 49 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር በሆነው አባይ ላይ የተመሰረተው ታላቁ የህዳሴ ግድቡ ከኢትዮጵያ አልፎ ለአህጉራዊ የጋራ ተጠቃሚነት የላቀ ትርጉም የሚሰጠው ነው። በጥናት እንደ ተረጋገጠው . . . ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በተለይም ለሱዳን ሕዝብ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የሚኖረው ይሆናል። በግብርናው ዘርፍ ሱዳናውያን በዓመት ሦስቴ እንዲያመርቱ፣ በሱዳን ከተሞች የሚደርሰውን የጎርፍ መጥለቅለቅን ለመቀነስ እና በዋነኝነት ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ የግድቡ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ነባሩን የቅኝ አገዛዝ እሳቤ መንፈስ፣ የውኃ ጂኦፖለቲካ ወዘተ ላይመለስ የደረመሰው የህዳሴ ግድብ ሙሌቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ከ70 በላይ (40 ያህሉ ብቻ ከ10 ሄክታር በላይ ይሸፍናሉ) ደሴቶች እንደሚኖሩት፤ ኢትዮጵያ ለዓለም ያበረከተችው ግዙፍ የመዝናኛ ስፍራ እንደሚሆን ከወዲሁ እየተነገረለት ያለ ሲሆን፣ ጉዳዩን ከመነሻው ያብራራ፣ የግንባታው ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ያዘጋጀው 14ኛ መደበኛ ጉባኤ ጳጉሜ 3 ቀን 2014 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል ተካሂዶ ነበር፡፡

በእለቱ የ2014 በጀት ዓመት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርትና የ2015 በጀት ዓመት ረቂቅ እቅድ ለጉባኤተኞቹ ቀርቦ በጥልቀት ውይይት ተካሂዶበታል፡፡

በጉባኤውም "የተለያዩ የልማት ስራዎችን በአንድነትና በትብብር ከሰራን ኢትዮጵያ የማታድግበት ምንም ምክንያት የለም" (የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አረጋዊ በርሄ) የሚል መሰረታዊ ሀሳብ ተላልፎበታል።

ሕዝቡን በከፍተኛ ደረጃ ለአረንጓዴ ልማት ያነሳሳው፤ የአገራችንም ስነ ምህዳር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲሻሻል፤ ለቴክኖሎጂም ሽግግር እገዛ በማድረግ ዜጎች በተግባር የተደገፈ ሰፊ እውቀትና ክህሎት እንዲያዳብሩ፤ እንዲሁም ቴክኖሎጂና ልምድ እንዲቀስሙ (የግድቡን ዲዛየን በማሻሻል እና የተርባይኖች አቅም በማሳደግ የግድቡ ኃይል የማመንጨት አቅም ከ5ሺህ 250 ወደ 6ሺህ 450 ያሳደጉት ዜጎች መሆናቸውን ልብ ይሏል) ያደረገው፤ የአገር ውስጥና የውጪ ቱሪዝምን በተለየ ሁኔታ የሚያበረታታው የህዳሴ ፕሮጀክት ለበርካታ ዜጎቻችን (በሸቀጣሸቀጥ፣ ምግብ፣ ትራንስፖርት በማቅረብ ተጠቃሚ የሆኑትን ሳይጨምር፤ ከ13ሺ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን፤ እንዲሁም፣ ከ400 በላይ ለሚሆኑ የውጭ ዜጎች - ከዚህም ሊበልጥ ይችላል) የስራ ዕድልን የፈጠረውን፤ የ3ኛውን ዙር ሙሌት መጠናቀቅን ተከትሎ አባይ ከባሕር ጠለል በላይ ከ600 ሜትር ከፍታ ላይ ይፈስ ዘንድ ያስቻለው መሆኑንና የመሳሰሉት የ2014 ወሳኝ ክንውኖች መሆናቸው ከላይ በጠቀስነው 14ኛው መደበኛ ጉባኤ (ጳጉሜ፣ 2014 ዓ.ም) ላይ መገለፁ የሚታወስ ነው።

**የሕዝብ ተሳትፎ**

በህዝቦች አስተሳሰብ ውስጥ የቁጠባ ባህልን እንዲዳብር እድል የፈጠረ፣ ቁጠባን ባህል ወደ ማድረግ (ግድቡ ሲጀመር አካባቢ የአገራችን የቁጠባ ባህል 5 በመቶ ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ አገራዊ ቁጠባችን 25 በመቶ አካባቢ ደርሷል) የመራው የህዳሴው ግድብ የሁሉን ድጋፍ ያተረፈ ፕሮጀክት ነው። ይህ ፕሮጀክት ሁሉም አገር ወዳድ ዜጋ የፖለቲካ አመለካከት፣ የሃይማኖት ልዩነት፣ የመኖሪያ ቦታ (ከአገር ውስጥም ይሁን ከውጭ) ርቀት ሳይገድበው፣ የብሄር፣ የዕድሜ ወይም የጾታ ልዩነት ሳይታይበት ሁሉም በአንድነት ሁሉአቀፍ ድጋፉን ቸሮታል። "ለዚህ ግድብ ድጋፍ ያላደረጉት ኢትዮጵያዊያን በማህጸን ያሉ ህጻናት እና በመቃብር ያሉ ሙታኖች ብቻ ናቸው" እስኪባል ድረስ ሁሉም የሚችለውን ሁሉ አድርጓል።

ከዚህ አኳያ፣ እኛ ኢትዮጵያውን ተደራራቢ ችግሮችን አልፈን ፕሮጀክቱ ዛሬ ላይ ለደረሰበት ደረጃ ማድረሳችን በብዙዎች በአድናቆትና አግራሞት እየተነገረ መሆኑ የአደባባይ እውነት ነው። የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎችም ሆኑ መንግስት ሕዝቡ ፕሮጀክቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ድጋፍ እንደሚያደርግ እምነታቸውን ሁሌም በመግለፅ ላይ መሆናቸውም እንደዛው።

8ሺህ ኪ.ሜ የሚሸፍን 2ኛው ዙር "የህዳሴ ግድብ ጉዞ 2" የሚል ስያሜ ያለው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃ ግብር ተጀምሮ በመካሄድ ላይ መገኘቱም ይህንን ህዝባዊ ተሳትፎ ከማጠናከር አኳያ ሲሆን፣ ስለሁኔታና ሂደቱ ከሚያትቱ ዘገባዎች መረዳት እንደተቻለው መርሀ ግብሩ በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

ሕብረተሰቡ ለዚህ ያለምንም የውጭ አገራት ብድር እና ዕርዳታ እየተከናወነ ለሚገኘው፣ አገራዊ ፕሮጀክት ያለውን አጋርነት የማጠናከር እና ገቢ የማሰባሰብ አላማ ያለው ይህ የጉዞ መርሐ ግብር (በመርሀ ግብሩ 200 ሚሊዮን ብር በተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ አማራጮች ለመሰብሰብ ታቅዷል) በከፍተኛ ደረጃ ህዝባዊ ንቅናቄ የተካሄደበት ሲሆን፣ በዚሁ ፕሮግራም (ለምሳሌ ያህል ማለት ነው) በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ብቻ በአንድ ቀን ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ የቦንድ ግዥ ተፈፅሟል።

የመርሀ ግብሩ ጉዞ 200 ከተሞችን የሚያዳርስ ሲሆን ከአዲስ አበባ ውጪ የሚያደርገው ፕሮግራም (የህዳሴ ግድብ ቱር 2፣ ኃብት ማሰባሰቢያ መረሃ-ግብር) ወደ አገሪቱ ሰሜን አቅጣጫ እንደሚያቀናም በወቅቱ መገለፁ የሚታወስ ነው። (የካቲት 2ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረው ይህ ፕሮግራም በታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት እና በኢትዮጵያ ታሪክ ባህል እና ቅርፅ አድን በጎ አድራጎት ድርጅት የተዘጋጀ ነው፡፡)

ከሶስት ዓመታት በኋላ (በ2017 ዓ.ም) ተጠናቆ የሚጠበቅበትን 6 ሺ 450 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት የሚጀምረውና የአገሪቱን 40 በመቶ የሃይል አቅርቦት የሚሸፍነው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት መጋቢት 2003 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ከአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት እንዲሁም ከልዩ ልዩ ገቢዎች በአጠቃላይ 17 ቢሊዮን 188 ሚሊዮን 444 ሺህ 565 ብር መሰብሰቡም ታውቋል፡፡

> **የታስቁ ህዳሴ ግድቡን የጎበኙት ሱዳናውያን ምሁራን "የታሳቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ የትብብር እንጂ የንትርክ መንስኤ ሲሆን አይገባም ።"**

13 ተርባይኖች ያሉት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ማስተባበሪ ጽህፈት ቤት በማህበራዊ (ፌስቡክ) ድረ-ገጹ (Grand Ethiopian Renaissance Dam) ላይ ኦገስት 24 2022 ለንባበብ እንዳበቃው ከሆነ፣ በሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም ብቻ 273 ሚሊየን 132 ሺህ 427ብር ተሰብስቧል፡፡ አርሶ አደሩም በጉልበቱ ከአንድ መቶ ቢሊዮን ብር እንደሚበልጥ የሚገመት ድጋፍ አድርጓል።

ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱ በ27/6/2015 እንዳስታወቀው "የቦንድ እና የፒን ሽያጭ በተሳካ ሁኔታ የተከናወነ ሲሆን ሕዝቡም ለታላቁ ህዳሴ ግድብ የቀረውን ግንባታ ለመጨረስ እስከ መጨረሻው ድጋፉን እንደሚቀጥል ቃል" ገብቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው "እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን!!!" ማለታችን ትክክል መሆኑን ነውና፣ በነካ እጃችን ሌሎች ግድቦችንም እንደምንቀጥል ከበቂ በላይ የሆነ ማሳያ ነው።

የኢትዮጵያ የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተወካይ ኃላፊ አቶ ሰለሞን ተካ እንደተናገሩት (ፌብሯሪ 22፣ 2023፣ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ) ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለበት ቀን ጀምሮ ማህበረሰቡን በማስተባበር ከ17ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን ጠቁመው በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት ከ868 ሚሊያን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉንም አያይዘው መግለፃቸውን፤ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ፍቅርተ ታምር በ2014 ብቻ በተለያዩ ገቢ ማሰባሰቢያዎች 1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ከኅብረተሰቡ መሰብሰቡን ስናክልበት ደግሞ የሕዝቡ ተሳትፎ ከ"ተአምር"ም ባለፈ ሰማይ ጠቀስ መሆኑን እንገነዘባለን።

ከላይ በጠቀስነውና በሸራተን አዲስ በተካሄደው ጉባኤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ 60 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ የፕሮጀክቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ክፍሌ ሆሮ ተናግረዋል። "የጋራ መገለጫ የሆነውን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድባችንን በማጠናቀቅ አሸናፊነትን ለትውልድ እናውርስ!፡፡" ለሚለው ጥሪም ሁላችንም ፈጣን ምላሽ ልንሰጠው ይገባልም ተብሏል። ይህም የህብረተሰቡ ያልተቋረጠ ተሳትፎ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን ያሳያልና "እንደ ጀመርነው እንጨርሰዋለን!!!" የሚለው እዚህም ይደገማል ማለት ነው።

**አስተያየቶች**

ኢትዮጵያ ስታስረዳ እንደ ቆየችው፣ ግድቡ ለጎረቤት እና እህትማማች አገራት ሁለንተናዊ ትስስር መጠናከር ወሳኝ ነው። የዓባይ ውኃ የተፋሰሱ አገራት የውጥረት ምክንያት ሳይሆን የልማት እና የትብብር መሆን ይገባዋል። አገራት በዚህ ዙሪያ ትኩረት ሰጥተው ከተንቀሳቀሱና የጋራ ተቋማዊ አደረጃጀት ከፈጠሩ የመልማት እድላቸው ሰፊ ነው። (ተቀማጭነቱን በሱዳን ካርቱም ያደረገው የአፍሪካ የአስተዳደር፣ ሰላም እና ሽግግር ጥናት ማዕከል ዋና ጸሐፊ ዶክተር ማህሙድ ዘይንላብዲን)

ባለፈው ነሀሴ የህዳሴ ግድቡን የጎበኙት ሱዳናውያን ምሁራን "የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ የትብብር እንጂ የንትርክ መንስኤ ሊሆን አይገባም።" ማለታቸው በየሚዲያዎች የተስተጋባ ሲሆን፤ የሌሎች ምሁራን ተመሳሳይ አቋምም እንደዚሁ ለአየር በቅቶ ሰምተናል።

ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል በተፋሰሱ አገራት መካከል እንዲነግስ የሚያደርገው፤ ከአገራት ጋር የመተማመንና የመተባበር ዲፕሎማሲን እንዲፈጠር ምቹ መደላድል የሚፈጥረው፤ ኢትዮጵያውያን ፍትሃዊ አመለካከትን የተላበስን መሆናችንን ለዓለም ለማሳወቅ ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረው፤ የአገራችንንም የመደራደር አቅም በከፍተኛ ደረጃ ያጎለበተው፤ የአገራችንን ገጽታ በመቀየሩ በኩል የማይተካ ሚናን የተጫወተው፤ ግብፅን ጨምሮ የታችኛው ተፋሰስ አገራት ለውይይት እና ምክክር በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲቀመጡ ያስቻለው፤ የተፋሰሱ አገራት የጋራ ሃብታቸውን በትብብር እና በመደጋገፍ ከመጠቀም ውጪ ሌላ አማራጭ እንደማይኖራቸው በግልፅ ያሳየው፤ አይቻልምን በይቻላል የቀየረው፤ ሲጠናቀቅ ከ1ሺህ 680 ኪሎ ሜትር ስኩዌር በላይ ስፋት የሚሸፍነው፤ በዓመት ከ10ሺህ ቶን በላይ ዓሳ የማምረት አቅምን የሚፈጥረው፤ ለሌሎች ታዳጊ አገራት ደግሞ በተፈጥሮ ሃብታቸው እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ መንገድን ያመላከተ (ያነቃቃም ጭምር)፤ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከዓለም ደግሞ ተጠቃሽ የሆነ ግዙፍ ግድብ፤ እንደመርግ የከበዱ ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን ተቋቁሞ ሁለተኛውን ኃይል ማፍለቅ የቻለው . . . ወዘተርፈ ታላቁ የህዳሴ ግድባችን በርካታ ውጫዊ መሰናክሎች ገጥመውት የነበረ ቢሆንም፣ ሁሉንም በጣጥሶ በማለፍ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ሊገኝ የቻለ ተአምረኛ ግድብ ነው።

ይህንን ሁሉ መሰናክል በማለፉም የበርካቶችን አድናቆት ሊያተርፍ የቻለ አኩሪ የሚሊኒየሙ ስኬት ለመሆን የበቃ ሕዝባዊ ኩራትና ብሔራዊ አርማ መሆኑም በበርካቶች ተመስክሮለታል።

**የግድቡ አሁናዊ ይዞታ**

የግድቡ ሁለተኛው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተርባይን ኃይል የማመንጨት ሥራን ለማስጀመር በተካሄደ ሥነ ሥርዓት ላይ ሥራ አስኪያጁ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ እንደገለፁት የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሥራ ወደ 83 ነጥብ 3 በመቶ፤ የግድቡ የሲቪል ሥራዎች ግንባታ 95 በመቶን፤ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራዎች ግንባታና እና ተከላ ወደ 61 በመቶ፤ የውሃ ማስተላለፊያ የብረታ ብረት ሥራዎችን ደግሞ 73 በመቶን የተሻገሩት ባለፈው ነሀሴ ወር ነው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የመንግሥትና የሕዝብ ሀብትን ከብክነት እየታደገ ያለው ‹‹ኢ-ጂፒ››

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አሁን አሁን ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም መረጃን በፍጥነትና በጥራት መለዋወጥ የተለመደ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተለይም ለመንግሥት ተቋማት ቀልጣፋ፣ ፈጣን፣ ጥራት ያለውና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት በመስጠት በኩል ጉልህ አስተዋጽኦ በማበርከት ተመራጭ እየሆነ መጥቷል። ከመንግሥት ተቋማት መካከልም ከፍተኛ መጠን ያለውን የመንግሥት ገንዘብ ለሚያንቀሳቅሰው የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን የሚኖረው አስተዋጽኦ የላቀ ሆኖ ተገኝቷል።

የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመንግሥት የግዥ ስርዓትን በኤሌክትሮኒክስ ማከናወን በመቻሉ የፌዴራል ተቋማት ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ከማግኘታቸው ባለፈ የግዢ ስርዓቱ ከሙስና የጸዳ እንዲሆን በማስቻል የአገር ኢኮኖሚን ከብክነት እየታደገ ይገኛል። በአሁኑ ወቅትም በርካታ የፌዴራል ተቋማት የፋይናንስ ግዥ ስርዓታቸውን በኤሌክትሮኒክስ መፈጸም በመቻላቸው ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ከሙስና የጸዳ ሥራ በመሥራት በኩል ለውጦች እያመጡ እንደሚገኙ መረዳት ተችሏል።

የመንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን እንዳስታወቀው 74 የሚደርሱ የፌዴራል ተቋማት የመንግሥት ግዥ ስርዓትን በኤሌክትሮኒክስ ተግባራዊ ማድረግ ችለዋል። ይህን ስርዓት በመተግበር አራት የፌዴራል ተቋማት የተሻለ አፈፃፀም ማሳየታቸው ተጠቁሟል፤ እነሱም የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ የቅርስና ጥበቃ ባለስልጣን፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ናቸው። ከእነዚህ አራት የፌዴራል ተቋማት መካከልም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የቅርስና ጥበቃ ባለስልጣን ተሞክሮዎቻቸውን በውይይት አቅርበዋል።

ኢ-ጂፒ የመንግሥትን ግዢ በቴክኖሎጂ አስደግፎ ዲጅታላይዝድ በማድረግ፤ አጠቃላይ ግዢ ሲፈጸም በኦን ላይን መፈጸም ማለት መሆኑን ያስረዱት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፤ የግዢና ንብረት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ፈጠነ ናቸው። ፍርድ ቤቱ፤ ኢ-ጂፒን ተቀብሎ በፍጥነት ወደ ተግባር መግባት እንደቻለና በዚህም ተጠቃሚ መሆኑን አቶ ሰለሞን ይጠቅሳሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የዳኝነት አገልግሎትን በአግባቡ በመደገፍና በማሳለጥ አገልግሎት ፈላጊውን ማርካት የሚል ግብ አስቀምጦ እየሰራ ነው።

ተቋሙ በራሱ ተነሳሽነት የመንግሥት ግዢን በኤሌክትሮኒክስ ለማድረግ ወደ ሲስተሙ ገብቷል። በዚህም ውጤት ማስመዝገብ እንደቻለና አገልግሎቱም ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ምቹ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል። በተለይም ለዳኝነት አገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በተገቢው ጊዜ በጥራትና በመጠን መድረስ እንዲችሉ በማድረግ ዘመናዊ የንብረት አስተዳደር እና የአጠቃቀም ስርጭትን አጠናክሮ ለማስቀጠል አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አቶ ሰለሞን ያስረዳሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ አሰራሩ ዕቅድን መሰረት ያደረገ የግዢና ንብረት አጠቃቀም ውጤታማነትን ከማረጋገጥ ባለፈ ከሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት የጸዳ ያደርገዋል። በሲስተሙ ያላለፈና ከዕቅድ ውጭ የሆነ ማንኛውም አይነት ግዢ በኢ-ጂፒ አይፈጸምም። በመሆኑም ኢ-ጂፒ አስቀድሞ ማቀድን የሚያስገድድ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በተቋሙ ውስጥ በዘፈቀደ የሚገዛ ግዢ በከፍተኛ መጠን መቀነስ ችሏል። ማንኛውም ጥያቄ ሲስተም ውስጥ ከሌለ ኢ-ጂፒ በፍጹም ሊያስተናግደው አይችልም፤ ይህም በእጅጉ ተመራጭ አድርጎታል።

ኢ-ጂፒ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በማጠናከር በተለይም የዘርፉን አደረጃጀት፣ የአሰራር ውጤታማነት ለማሻሻልና ለማዘመን አይነተኛ ድርሻ እንዳለውም ነው የተናገሩት። በዚህም ኪራይ ሰብሳቢነትን ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ባይቻልም መቀነስና ማቀጨጭ መቻሉን ያነሱት አቶ ሰለሞን፤ ይህም በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት መስጠት እንዳስቻለ ነው የተናገሩት።

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዢ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ በመቻሉ ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ እንደቻለ የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ በተለይም የተቋሙን የግዢና ንብረት ዕቅድ ለማዘጋጀት ያለው አቅም በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል ብለዋል። በዚህም ተቋሙ ዲጂታል የግዢና ንብረት አስተዳደር የአሰራር ደረጃ ላይ መድረሱን ተናግረው፣ ይህም በተግባር የሚታይ እንደሆነ ነው ያስረዱት። በአሁኑ ወቅትም ከሲስተም ውጭ የሚገዛ ንብረት በተቋሙ እንደሌለ ጠቅሰው፣ ዕቃ ሲገዛም ሆነ ሲወጣ በሲስተሙ አማካኝነት ግልጽ በሆነ መንገድ ነው ይላሉ።

**ተቋሙ በአሁኑ ወቅት ኢፍሚስ እና ኢ-ጂፒን መጠቀም በመቻሉ በግዢ ስርዓቱ ላይ ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት ችሏል። በተለይም ባለሙያዎች በግዢ ዘዴ መረጣ ላይ ያላቸው ዕውቀት በመጨመሩ ሥራውን በሚገባ መሥራት የሚችሉ ብቁ ባለሙያዎች እንዲሆኑም አድርጓቸዋል**

በተቋሙ የግዢ ስርዓት ላይ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በ2013/14 ዓ.ም ጥናት ማድረጉን ያስታወሱት አቶ ሰለሞን፤ በዚህም ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አበረታች ውጤት ማምጣት የቻለ ተቋም መሆኑን ማመላከቱን ተናግረዋል። ተቋሙ በአሁኑ ወቅት ኢፍሚስ እና ኢ-ጂፒን መጠቀም በመቻሉ በግዢ ስርዓቱ ላይ ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት ችሏል። በተለይም ባለሙያዎች በግዢ ዘዴ መረጣ ላይ ያላቸው ዕውቀት በመጨመሩ ሥራውን በሚገባ መሥራት የሚችሉ ባለብቁ ባለሙያዎች አድርጓቸዋል ሲሉ ያብራራሉ።

ባለሙያዎቹ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት፣ በመገምገምና በመተንተን አጠቃላይ የግዢ ስርዓቱ ደረጃውን ያሟላ መሆን እንዲችል አድርገዋል። በዘርፉ የግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ መመሪያ፣ የጨረታ ሰነዶች፣ የአሰራር ሥርዓቶችን በማሻሻል ዓለም ወደ ደረሰበት የዲጅታላይዜሽን ወይም ኢፍሚስ፣ ኢ-ጂፒ፣ ኢገቨርመንት የሚባሉ የአሰራር ስርዓቶችን ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን የገለጹት አቶ ሰለሞን፤ በቀጣይም ፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚታዩ በርካታ ችግሮችን መቅረፍና የገጽታ ግንባታውን መቀየር የሚቻለው በአገር ልጆች የለማውን ኢ-ጂፒ ቴክኖሎጂን መጠቀም ሲቻል ነው ብለዋል።

በተለይም ፈጣንና ጥራት ያለው እንዲሁም ከሙስና የጸዳ አገልግሎት ለመስጠት የጀርባ አጥንት የሆነውና ትልቁ የአገሪቷ በጀት የሚውለው ግዢ ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህም ግዥ ላይ መሥራት አስፈላጊና ወሳኝ እንደሆነ አስረድተዋል።

በአፍሪካ 13 ትሪሊየን የአሜሪካ ዶላር ለግዢ ብቻ ወጪ የሚደረግ መሆኑን ለአብነት የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ ይህን ከፍተኛ የአገሪቷን ወጪ የሚጠይቀውን ግዢ በአግባቡ፣ በስርዓትና በዕቅድ ለመመራት በቴክኖሎጂ መደገፍ የግድ ነው ይላሉ። ያ ካልሆነ ግን የሚመጣው ኪሳራ ከባድ መሆኑን ጠቁመው፣ በመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ስርዓት ያልገቡ የፌዴራል ተቋማት በፍጥነት ወደ ሲስተሙ ገብተው ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር አገሪቷን ከሀብት ብክነት መታደግ እንዲችሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን የግዢና ፋይናንስ ዳይሬክተር አቶ ማሞ አሸብር በበኩላቸው የባለስልጣኑ ዋና ሥራ ቅርሶችን መመዝገብ፣ መጠበቅ፣ መንከባከብና ለትውልድ ማስተላለፍ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህን ተግባራዊ ለማደረግም በቴክኖሎጂ የታገዘና ቀልጣፋ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ወሳኝ ነው ይላሉ። ፈጣን፣ ቀልጣፋና ግልጽ የሆነ የአሠራር ስርዓትን መከተል የሚያስችለው የኢ-ጂፒ ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ባለስልጣኑ ሥራውን እያሳለጠ እንደሆነም አስረድተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የተቋሙን የግዢ ስርዓት ቀልጣፋና ፈጣን ከሰው ንክኪ ነጻ ለማድረግ የመጀመሪያው ሥራ የዕቅድ ዝግጅት ነው። ከዕቅድ ዝግጅት ውጭ የሚደረግ ግዢ አይኖርም። ይሁንና ከዚህ ቀደም በነበረው የአሰራር ስርዓት ከዕቅድ ውጭ በሆነ መንገድ የተለያዩ ግዢዎች በዘፈቀደ ይከናወኑ ነበር። በመሆኑም ዛሬ አንዱ ዳይሬክተር አንድ ነገር እንዲገዛለት ይጠይቃል። ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲሁ ሌላው የፈለገውን ዕቃ የሚያስገዛበት ሂደት ነበር። ይህም የሀብት ብክነትን ከማስከተሉም ባለፈ ለከፍተኛ ኪራይ ሰብሳቢነት ሲዳርግ ቆይቷል።

በአሁኑ ወቅት ግዢ የሚከናወነው ቴክኖሎጂን በመጠቀም ኢ-ጂፒን ተግባራዊ በማድረግ ነው ሲሉ ዳይሬክተሩ ይገልጻሉ። ኢ-ጂፒ ደግሞ በዕቅድ ያልተያዘና ያልታቀደ ግዢን የማይቀበል በመሆኑ ፍላጎትን መሰረት በማድረግ የመንግሥት ግዢው በኢ-ጂፒ እንደሚከናወን ይናገራሉ። በቅድሚያ በተቋሙ ውስጥ ያሉ የሥራ ክፍሎችን በሙሉ በየዘርፉ በመከፋፈል ስለትክክለኛነቱ በማጥራት ለግዢ ኮሚቴ እንደሚቀርብ፣ የቀረበው የግዢ ፍላጎትና የሥራ ክፍሎቹ ትክክለኛ ስለመሆናቸውም በኃላፊዎች እንደሚረጋገጥ ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ባለስልጣኑ ቅርስን ጠብቆና ተንከባክቦ ለትውልድ በማስተላለፍ ሂደት ውስጥ ለሚያከናውናቸው ተግባራት አሸዋ፣ ድንጋይና አፈር ሳይቀር ይገዛል። ይሁንና እነዚህ ግብዓቶች ከዚህ ቀደም በማኑዋል ሲገዙ የነበረ ሲሆን፤ የግዢ ስርዓቱም ለከፍተኛ የሀብት ብክነትና ለብልሹ አሰራር ተጋልጦ ነበር።

በአሁኑ ወቅትም እነዚህ ግብዓቶች በመንግሥት የግዢ ስርዓት ውስጥ መካተታቸውን ጠቅሰው፣ ማንኛውንም ግዢ በኢ-ጂፒ መግዛት እንደሚቻል መረጋገጡን ተናግረዋል። ወደ ሥራው በመግባት ትርጉም ያለው ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን አመላክተዋል።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኢ-ጂፒ ሲስተምን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ በመቻሉ በዘርፉ ያካበተውን መልካም ተሞክሮ ለሌሎች ተቋማት እያካፈለ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ይሁን እንጂ ኢ-ጂፒን ተግባራዊ ሲያደርግ የተለያዩ ፈታኝ የሚባሉ ችግሮች አጋጥመውት እንደነበር ያነሱት አቶ ማሞ፤ ነገር ግን ችግሮቹን ያለመታከት የማንዋሉን የግዢ ዘዴ ለማስቀረት ቴክኖሎጂውን በመጠቀም የኢ-ጂፒ የአሰራር ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ እንደቻሉ ነው ያስረዱት።

የመንግሥት ሥራን ለመሥራት አንዱና ዋነኛው ክንፍ ግዢ እንደሆነ የገለጹት የፌዴራል ግዢ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ወልደአብ ደምሴ፤ በበኩላቸው ከግዢ ውጭ የሚሠራ ሥራ የሌለ መሆኑን ይናገራሉ። ከ60 እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው የመንግሥት ገንዘብ ለመንግሥት ሥራ የሚውል መሆኑን ያመለክታሉ። ለመንግሥት ሥራ የጀርባ አጥንት የሆነው የመንግሥት ግዢ በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥርዓትን ተከትሎ እንዲሰራ የሚደረገው ጥረት የመንግሥትና የሕዝብን ሀብት ከብክነት ከመታደግ ባለፈ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ያስችላል። የመንግሥት ግዢን በቴክኖሎጂ ሲታገዝና ዘመናዊ የአሰራር ስርዓትን ሙሉ ለሙሉ ሲከተል በኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ድርሻ የጎላ እንደሆነ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ግዢ የሚፈጸምባቸው የአሰራር ስርዓቶች አሉ። ከእነዚህ የአሰራር ስርዓቶች አንዱ ግልጸኝነት ነው። ግልጸኝነቱ የሚረጋገጠውም አራተኛው መንግሥት ተብሎ በሚታወቀው በሚዲያው በመሆኑ በተለይም ሚዲያው ግዢ ላይ የሚታዩ ለውጦችን ወደ ሕዝቡ በማድረስ በኩል ጉልህ ድርሻ አለው። ስለሆነም ሚዲያው እንደ አራተኛ መንግሥትነቱ በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ መደገፍና ማጋለጥ ይጠበቅበታልም ብለዋል።

የመንግሥትን ግዢ በቴክኖሎጂ አስደግፎ ዲጂታላይዝድ በማድረግ ግዢ ሲፈጸም በኦን ላይን መፈጸም ከተቻለ በመልካም አስተዳደር በኩል ያለውን ከፍተኛ ችግር ማቃለል እንደሚቻልም አስታውቀዋል። የመንግሥት ግዢን በኢ-ጂፒ መተግበር ያስፈለገበት አንዱ ዓላማም መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣ ለሚወጣው ወጪ ተመጣጣኝ ውጤት ማስገኘትና ለአገሪቷ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ድጋፍ ማድረግ ነው ይላሉ።

መንግሥት ትኩረት ከሰጣቸው ዋነኛ የሥራ ዘርፎች አንዱ የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት ሲሆን፤ በዚህም ኢትዮጵያ በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ስርዓት በመተግበር ከአፍሪካ በስድስተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኑን ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ከዛሬ አራት ዓመት በፊት የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ስርዓት አሁን ላይ 74 የፌዴራል ተቋማት የፋይናንስ ግዥ ስርዓታቸውን በኤሌክትሮኒክስ መፈፀም ችለዋል። በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ 726 ጨረታዎች በኤሌክትሮኒክስ ተፈጽመዋል። ጨረታዎችን ለመሳተፍ ከክልል ከተሞች ወይም ከሌሎች አገራት የሚደረገውን ጉዞ በማስቀረት ዜጎች የሥራ ጊዜያቸውን ሳያባክኑ ወጪያቸውን ማዳን ችለዋል። ከሁሉም በላይ በዘርፉ የሚካሄደውን የሙስና ሰንሰለት ቆርጦ መጣል ያስቻለ እንደሆነም ተገልጿል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ያልተፈታው የመብራት አገልግሎት

ክብረአብ በላቸው

ኢትዮጵያ በአላት አቅም የኃይል አቅርቦትን ለዜጎቿ ተዳራሽ ለማድረግ ሰፊ ስራዎችን ስትሰራ ቆይታለች። ነባር የመብራት መስመሮች እድሳት፣ እንዲሁም፣ የአዳዲስ መስመሮች ዝርጋታ በስፋት ተከናውኗል። በዚህም የኤሌክትሪክ ኃይል ተዳራሽ ባልሆነባቸው የተለያዩ የገጠር መንደሮች ጭምር ይሄንን የኃይል አቅርቦት ለመድረስ ጥረት ተደርጎ ብዙ ዜጎች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

ነገር ግን ዜጎች፣ በተለይም የከተማ ነዋሪዎች፣ በዚህ ጉዳይ ያላቸውን ቅሬታ በተደጋጋሚ ያነሳሉ። ተደራሽነቱ ፍትሃዊ አይደለም፤ ይህ ነው ሊባል በማይችል ሁኔታ አቅርቦቱ ይቋረጣል፤ እና መሰል ጥያቄዎችን ያነሳሉ። ይህም፣ የዜጎች ሕዝባዊ አገልግሎትን የማግኘት ሰብዓዊ መብት፣ በመላ ሀገሪቱ የአገልጋይ ተቋሙ የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ ቆይቷል። ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት ለጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት የተለያየ ምላሽ ሲሰጥ ኖሯል። ዛሬም ድረስ ግን ችግሩ አልተቀረፈም። በአዲስ አበባ ደግሞ ችግሩ በስፋት ይስተዋላል፤ ተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥም የእለት ተእለት ገጠመኝ ነው። ይህም ነዋሪዎችን ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ሲዳርጋቸው ይታያል።

ወይዘሮ ለምለም አፈወርቅ (ስማቸው የተቀየረ) በአዲስ አበባ፣ በተለምዶ "ጀሞ አንድ" ተብሎ የሚጠራው ኮንደሚኒየም ሰፈር ነዋሪ ናቸው። እሳቸው እንደሚናገሩት፤ እነሱ አካባቢ ያለው የመቆራረጥ ችግር ብቻም አይደለም። አንድ ጊዜ ከጠፋ አይመለስም። አንድ ሙሉ ቀን ወይም ለሁለት ቀናት ሳይመጣ ይቆያል። በዚህም እየተጋፈጥን ያለው ችግር ብዙ ነው። በዚህ ጊዜ ደግሞ መብራት ብርሃን ከመስጠት ባለፈ አገልግሎቱ ዘርፈ ብዙ ነው። ይህንን ሁሉም ሰው ያውቃል። ድርጅቱም ያውቃል። አብስለን ለመመገብ፣ እንጀራ ለመስራት ተዘጋጅተህ ይጠፋል። መብራት ያለመኖሩ ወይም መቆራረጡ ይሄንን ሁሉ ኪሳራ ነው እያመጣብን ያለው። በዛሬ ኑሮ ውድነት ደግሞ አስበው።

ሌላዋ ያነጋገርናቸው ቅሬታ አቅራቢ የዚሁ ኮንደሚኒየም ሰፈር ነዋሪ ናቸው። እንደ እሳቸው ብሶት አዘል ማብራሪያ የችግሩ ጫና ይበረታል፤ ከአቅም በላይም እየሆነ ነው። ይህ እንደለ ሆኖ፣ በችግሩ ምክንያት ቤት መስራት ሳይቻል ይቀርና ከውጭ ለመግዛት ሌላ አማራጭ ሲፈለግ፣ በአካባቢው በአጠቃላይ መብራት ስለማይኖር፣ እንጀራ በብርህ ለመግዛት ስታማትር ድሮ የሚሸጥበት ቦታ ሁሉ አይኖርም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የእንጀራ ሻጮቹ ሳይሆን፣ እነርሱም ጋር ኃይል መቆራረጥ መኖሩ ነው።

ሌላው ደግሞ ትንሽ ዝናብ ጠብ ባለ ቁጥር መብራት የመቋረጡና ችግር የመፈጠሩ ጉዳይ ነው። መብራት ሲጠፋ፣ ቅድመ ጥንቃቄ እንዳናደርግ ሳይነገረን ነው እልም የሚለው። ይሄ ትልቅ ችግር ሆኖብን ነው ያለው።

ከላይ በቀረቡት የኃይል ተጠቃሚዎች ቅሬታ መነሻነት "የመብራት መቆራረጥ ዛሬም ችግር ሆኖ ዘልቋል። እስከ ዛሬ ከተለመደው ምላሽ ውጭስ የተሻለ መፍትሔ ነው የሚባልስ አለ ወይ?" ሲል አዲስ ዘመን ለሚመለከተው አካል ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ሲሆን፤ የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ገበየሁ ሊካሳ ምላሽ ሰጥተዋል።

የተለመደ መልስ ለሕዝብ አንሰጥም የሚሉት ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ገበየሁ ሊካሳ፣ የኃይል መቆራረጡን በተመለከተ ከመነሻው ለማስረዳት የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ደካማ ነበር። 1990ዎቹ ላይ 400 ሜጋ ዋት ኃይል ነው የነበረን። ስለዚህ መንግስት እስትራቴጂካሊ ለኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ቅድሚያ ሰጥቶ፣ ከፍተኛ ፋይናንስ መድቦ ብዙ ስራዎችን ሰርቷል። ከየትኛውም ሴክተር በበለጠ ኤሌክትሪክ ላይ ነው ሀብት የፈሰሰው። በዚህም አሁን ያለን የኃይል ማመንጫ አምስት ሺህ ሜጋ ዋት ደርሷል። ይህ ከሁለት አመት በኋላ አስር ሺህ ሜጋ ዋት ይደርሳል። ይህ ከእኛም ተርፎ ለጎረቤት ሀገራት የሚተርፍ ነው የሚሆነው። በዛው ልክ



ዶክተር ገበየሁ ሲካሳ

በማከፋፈያ ከተሞች አካባቢ ያለው የማከፋፈያ ኔትዎርክ አልተሰራም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቅድሚያ ለኃይል ግንባታ በመሰጠቱ ነው። ወደ ከተሞች አካባቢ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በተጠናከረ ሁኔታ እየሰራን ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ሁለት ምዕራፎች ያሉት ፕሮጀክት ተጠናቋል። በአጠቃላይ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር የመካከለኛ ቮልቴጅ፣ አምስት ሺህ ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፤ እንዲሁም፣ አስር ሺህ አምስት መቶ የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮች አሉ። እነዚህ ያረጁ ናቸው። ሌላ ነገር ብናወራ ጥቅም ስለሌለው ወይም ደግሞ ይህንን ኔትዎርክ በሙሉ በአንድ እና በሁለት አመት በማሻሻል እናጠናቅቅ ቢባል የማይቻል ስለሆነ ከእውነት ውጭ እንሆናለን። ፋይናንስ ከማግኘት ጋርም ሆነ መሬት ላይ ከመተግበር ጋር ቀደም ሲል የሰራናቸው የማሻሻያ ስራዎች ቢኖሩም፤ ቀደም ሲል የባቡር መስመር ሲዘረጋ የኃይል መስመሮቹን በጣጥሷቸዋል። በዚህ ምክንያት ነው በ2011 ዓ.ም ከአሮጌ ኔትዎርክ የጀመርነው። ይህንን የምናገረው ለምን ከዛ በፊት አልተሰራም ያልከውን ለማስረዳት ያህል ነው።

አንደኛ በኃይል ግንባታ ላይ ቅድሚያ ስለተሰጠ ነው። ሁለተኛ ከ2003 እስከ 2011 ድረስ በሜቴክ ኮንስትራክሽን ምክንያት የዕቃ አቅርቦት እጥረት በመኖሩ ነው። ቃል በቃል ለመናገር ያረጀ ኔትዎርክ ነው የነበረው።

2011 ዓ.ም ላይ ይህን ሁለት ሺህ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር የመካከለኛ ቮልቴጅ፣ አምስት ሺህ ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፤ እንዲሁም፣ አስር ሺህ አምስት መቶ የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮችን ስትራቴጂ በመቅረፅ፣ በአራት ምዕራፎች ተደራሽ ለማድረግ ፕሮጀክት ተነደፈ። የመጀመሪያው ፕሮጀክት "የስምንቱ ከተሞች ፕሮጀክት" ይባላል። 2011 ዓ.ም ላይ ተጀምሮ 2013 ዓ.ም ላይ ነው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀው። ይህ ፕሮጀክት የክልል ዋና ዋና ከተሞችን እና አዲስ አበባን የሚያጠቃልል ነው።

በዚህ ስራ አዲስ አበባ ላይ 40 ኪሎ ሜትር መካከለኛ ቮልቴጅ፣ 412 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፣ 82 የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮች እና 15 ማስተላለፊያ ጣቢያ (switching station) ነው የተሻሻለው። ሁለተኛው ምዕራፍ በ2012 ዓ.ም ተጀምሮ 2014 ዓ.ም ላይ ተጠናቀቀ። በዚህ ደግሞ 725 ኪሎ ሜትር የመካከለኛ ቮልቴጅ፣ 400 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፣ 400 አገዥ የማከፋፈያ ትራንስፎርመር እና 73 switching station በዋናነት ተሰራ። ተመርቆም አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

ሶስተኛው ምዕራፍ ባለፈው በጀት አመት ነው የተጀመረው። በዚህ በጀት አመት መጨረሻ ላይ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቅ ነበር። በተለያየ ምክንያት በኮረና፣ በኮንቴነር እጥረት ሳይጠናቃቅ ቆይቷል። በዚህ ስራ ደግሞ 733 ኪሎ ሜትር መካከለኛ ቮልቴጅ፣ 400 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ ቮልቴጅ፣ 258 አጋዥ የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮች፤ ሰብ ስቴሽኖች እና የመቆጣጠሪያ ጣቢያን ጨምሮ አሁን እየተሰራ ነው የሚገኘው። 2016 ዓ.ም ላይ ይጠናቀቃል።

የዚህ ስትራቴጂክ ዕቅድ አራተኛው እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ 600 ኪሎ ሜትር መካከለኛ ቮልቴጅ፣ ቀሪውን በሙሉ ማለት ነው፣ 2000 የማከፋፈያ ትራንስፎርመሮች አሉት። 2017 ዓ.ም ላይ ይጠናቀቃል። የአማካሪ ቅጥር እና የጨረታ ሂደት ተጀምሯል። ይሄን ስራ ስትራቴጂ ነድፈን በትክክል እየተመራ ነው የሚገኘው። ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስራ ነው እየተሰራ ያለው። ለምሳሌ የመስመር ዝርጋታው በመሬት ስር ይካሄደል። በኮንክሪት ምሰሶ ነው የሚሰራው፣ ሽፍን ሽቦ ነው የምንጠቀመው። ይህ የኃይል መቆራረጡን ይቀርፋል። በዚህ ሂደት በተጠናከረ ሁኔታ አሮጌውን ኔትዎርክ ለመቀየር በስፋት እየሰራን ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ለምለም ሁሉም ቦታ ሲጠፋ ይሄ በቂ በሆነ ምክንያት የሆነ ነው። እንደ ሀገር ያለ ችግር ነው ተብሎ መቀበል እንዳይቻል አንድ ሰፈር፣ አስፋልት ተሻግሮ፣ ማዶ መብራት ይኖራል። እዚህ ጋር ደግሞ አይኖርም። "ይህ ለምን ይሆናል?" ተብሎ ቢጠየቅም ምላሽ የሚሰጥ ማንም የለም ይላሉ።

ዶ/ር ገበየሁ በበኩላቸው ይሄ የሚሆነው አንደኛው ትራንስፎርመር ለተወሰነ ደንበኛ ነው አገልግሎት የሚሰጠው። እሱ ላይ ችግር ሲፈጠር ያ ሰፈር መብራት ያጣል። ሄደን እስክንጠግን ድረስ በዛ መስመር ብልሽት ካለው መስመሩ አገልግሎት አይሰጥም። ሌላው ግን ያገኛል። እናም በዚህ ምክንያት በኔትዎርኩ ነባራዊ ሁኔታ የሚፈጠር ችግር እንጂ ልዩነት ለመፍጠር ታስቦ የተሰራ ስራ አይደለም። በአካል ሄደን አይተናል። ማሻሻያ ያደረግንባቸው መስመሮች በሰሞኑ የአየር ሁኔታ እንኳ አልተጎዱም። በዚህ ደረጃ፣ እስትራክቸርድ በሆነ ፌዝ፣ በተጠናከረ መልኩ እየሰራን ነው። ግን ስንሰራ ችግሮች ያጋጥሙናል። የከተማው ማስተር ፕላን አሁን እየተተገበረ ነው። "እነዛን ኔትዎርኮች አንሱ" የሚል ይመጣል። እነርሱን እናነሳለን።

ከሌሎች የመሰረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ጋር በቅንጅት የመስራት ችግር ስለመኖሩ፤ ይሄንን ችግር ለመቅረፍስ ምን እየሰሩ እንደሆነ ጠይቀናቸው ዶ/ር ገበየሁ ሲመልሱ፤

አዲስ አበባ አዲስ ማስተር ፕላን አለው። እንደገና ፈርሰው የሚሰሩ፣ በጣም አሮጌ ሰፈሮች አሉ። ጎን ለጎን መሰረተ ልማት እየተስፋፋ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች ደግሞ ቴሌ ስራ አለው። ውሃም አለው፤ መብራትም አለው። እነዚህ ካልተቀናጁ ስራው በአግባቡ ሊመራ አይችልም። በምንም ተዓምር።

ከአዲሱ የመንግስት ርፎርም በፊት፣ አዳዲስ በሚሰሩ መንገዶች ላይ በሙሉ ከ2006 እና 2007 ዓ.ም ጀምሮ ችግሩ በስፋት ነበር። አሁን ቅንጅቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል። አሁን የመሰረተ ልማት ቅንጅት የሚባል ተቋም አለ። በዚህ መልኩ በተሰራው ስራ ለውጥ ተይቷል። ይሁን እንጂ፣ በብዙ ምክንያት በአንድ ምሽት ችግሩን መቅረፍ ደግሞ አይቻልም።

ወይዘሪት ብዙነሽ አለሙ በአዲስ አበባ በአንድ አካባቢ በፈጣን ምግብ አቅርቦት ቢዝነስ ስራ ላይ የተሰማራች ወጣት ናት። እርሷ እንደምትናገረው፤ የመብራት መቆራረጥ በእጅጉ እየተፈታተናት ይገኛል። አለ ስትል የለም። "ደንበኛ መጥቶ ምግብ እያበሰልኩ ይጠፋል። የጀመርኩትን ምግብ ለመጨረስ ደግሞ ከሰል በማያዋጣኝ ዋጋ ገዝቼ ካቀጣጠልኩኝ በኋላ መብራቱ ይመጣል። እንደገና ደግሞ ተመልሶ ይጠፋል። በዚህ ምክንያት ደንበኛም ይሰለቻል። ሌላ አማራጭ ወደ መፈለግ ይሄዳል። ይሄ ፈተና ሆኖብኛል። በተጨማሪም በዚህ የኃይል መቆራረጥ ምክንያት የማብሰያ ስቶቬ ተቃጥሎብኝ ያውቃል። ቤት ተከራይተን ነው ስራችንን የምንሰራው። በየወሩ ለመብራቱም እንከፍላለን። ይሄም በሚሰራው ስራ ውጤታማ እንዳልሆን እያደረገኝ ነው። በዘላቂነት ችግሩን መፍታት ለምን እንደማይቻል አይገባኝም" ስትልም የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ትገልፃለች።

እንደ ዶ/ር ገበየሁ ማብራሪያ ከሆነ ዘላቂ መፍትሔው የሚገኘው ቅድም በጠቀስኩት አራተኛው ምዕራፍ፣ 2017 ዓ.ም ላይ በሚጠናቀቀው ፕሮጀክት ነው። ይሄ ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ያግዘናል። ሰሞኑን የተከሰተው የኃይል መቆራረጥ ደግሞ ካልተጠበቀው የአየር ሁኔታ የመጣ ነው። ሁለተኛው እና ትልቁ ችግር አራቱንም ምዕራፎች ስንሰራ አሮጌውን መስመር በአንድ መንገድ ላይ ትተን በሌላው አይደለም የምንሰራው። ኮሪደር የለም። ከተማ ውስጥ እያጠፋን ነው ሌላውን የምንሰራው። በዚህ ምክንያት ኮንክሪት ተክለን እስኪደርቅ እንጠብቃለን። ኢንሱሌተር እናሰራለን። ያኔም ይጠፋል። እና ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈፀም ሲባል የሚጠፋው ኤሌክትሪክ ነው የሚበዛው።

ማሳወቅን በተመለከተም "ሳይነግሩን ነው የሚያጠፉት" የተባለው ስህተት ነው። የመስመር ማሻሻያ ስራ ሲኖር በሁሉም የሚዲያ አማራጮች ለኅብረተሰቡ እናሳውቃለን" በማለት መልሰዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች




እታገኝ አሰፋ



ዳንኤል ብርሃኑ



ደሴት አበበ



ዱረቲ ታደሰ

## ሴቶች በማስታወቂያ ውስጥ የሚሳሉበትን ያልተገባ ምስል የማስተካከል ትጋት

**ሰላማዊት ውቤ**

ማስታወቂያ መልክ በመጠየቁና የገቢ ምንጭ በመሆኑ ሴቷም የግድ ተፈጥሮ በቸረቻት ውበት ተጠቅማ የዚህ ፀጋ ተቋዳሽ በመሆኗ ብዙዎች ይስማማሉ።ማስታወቂያ በማስተዋወቅ ሰበብ ሴትነትንና ውበትን እንደ ሸቀጥ ማቅረብ፤ ደግሞ ሲያከራክር ይደመጣል።በመገናኛ ብዙሃን በሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ከፊል የሴት እርቃንን፤ ቅርጽና ውበትን ጨምሮ፤ የቤት ውስጥ ሥራ ለሴቷ ብቻ የተሰጠ የሚያስመስሉ ያልተገቡ መልዕክቶች ሲተላለፉ ይስተዋላል። መልክቶቹ በአገራችን ከማህበራዊ ሚዲያዎች መስፋፋት ጋር ተደማምረው ታዳጊዎችን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያመሩ እያደረጉ ይገኛሉ። በተለይ የነዚሁ ማስታወቂያዎች መልዕክትና ይዘት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጾታዊ ጥቃቶችን ለማባባስም ኢትዮጵያ በስርዓተ ጾታ ዙሪያ የገባቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እየተገበረች ያለችበትንም ሂደት ቀደም ሲል ማህበረሰቡ በተዛባ አስተሳሰብ ምክንያት የወንድ የሴት ብሎ ከፋፍሏቸው ወደ ነበሩ ዘመናት ይመልሳል ተብሎ ያሰጋል።

ባለፈው ሳምንት እንዲህ ዓይነቱን ተግባር በመገናኛ ብዙሃን የሚያስተጋቡ አካላትን የሚከታተልና የሚቆጣጠር አካል ያለ አያስመስልም የሚሉ አስተያየቶችን አስተናግደን ነበር።ለዛሬም የማስታወቂያ ሠራተኞችና አስተላላፊዎች እንዲሁም ተቆጣጣሪና ባለድርሻ አካላትን ያካተተ አስተያየት ይዘን ቀርበናል።

‹‹ማስታወቂያ መልክ ይጠይቃል›› የምትለው የካፌ ኢንዱስትሪ ፈር ቀዳጇ ፀደይ አስራት በ17 ዓመቷ ወደ ፋሽን ኢንዱስትሪ መግባቷን ትናገራለች።ከመድረክ ጀምራ እስከ መገናኛ ብዙሃን በመዝለቅ የልብስ ፋሽኖችንና የተለያዩ ማስታወቂያዎችን ስትሰራ ቆይታለች።‹‹ፋሽን ለመከተል የግድ ፋሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ መሆን የለብኝም››ስትል ፋሽንና ውበትን እንደ ፊቱ የገቢ ምንጭ ባታደርገውም ከራስ ፀጉር እስከ ጥፍር አምሮ መታየት ማንኛዋም ሴት የምትፈልገው እንደመሆኑ እኔም በግሌ እቀጥልበታለሁ እንጂ የፈለገ ቢሆን አልወጣበትም ትላለች። ሥራው ከመልክ በተጨማሪም የተሻለ አስተሳሰብና በራስ መተማመን እንደሚጠይቅም እሷ ባለፈችበት ወቅት ወደ ሥራው የምትገባ ሴት እነዚሁ ጥያቄዎች ትጠየቅ የነበረ መሆኑን በማሳያ ታነሳለች።ቢሆንም አካል የሚገላልጥና ግላዊ ስብናና ክብርን የሚነካ ሴትነትን መጠቀሚያ የሚያደርግ ማስታወቂያ ሴቷ እንድትሰራ ማድረግ አግባብ አለመሆኑን ታወሳለች።

ማስታወቂያ ውበት ይፈልጋል።ውበት ደግሞ በሴት ይገለፃል” የሚሉት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እታገኝ አሰፋ ሴቶች በውበታቸው በማስታወቂያ በመሳተፍ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። “ማስታወቂያ ሀብት ነው።ትልቅ የገቢ ምንጫችንም ነው። እንደ አገር ሴቶች ከዚህ ተነጥለን ብቻችንን ምንም አናደርግም። ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ሁሉንም ያሳያል። በውጭ ማስታወቂያዎችም ቆንጆ ሴቶች ተመርጠው ነው የጽዳትና ውበት መጠበቂያ ግብዓቶችን ሲያስተዋውቁ የምናየው”ይላሉ። ሴቶች በእድገት ጎታችና ሐይማኖታዊና ባህላዊ እንዲሁም የግል ስብእና እና ክብር በሚነኩና በሚሸረሽሩ ማስታወቂያዎች እንዳይሳተፉ ከልብ ከተፈለገ መጀመሪያ አናናራችንን ማስተካከል አለብን ይላሉ።ለምን ቢባል ልብስ ማጠብ፤ ልጅ መንከባከብ፤ ማሳከም በደምሳሳው የቤት ውስጥ ሥራ ዛሬም ድረስ በሴቶች እየተሰራ ያለ የእውነታው ነፀብራቅ ከእውነታው የራቀ ማስታወቂያ ተቀባይነት የለውም ባይ ናቸው።በመሆኑም አናናራችንን ላይ ሥራ ሳንሰራ ሴት ሁልጊዜ እንዴት ልብስ አጣቢ ብቻ ሆና በማስታወቂያ ትሳላለች የሚለውን ከወሰድን ይቸግራል።መፍትሄው ወንዶች የሴቶችንም ሥራ እየሰሩ፤ ሴቶች የወንዶችንም ሥራ እየሰሩ ልክ እንደ አውራምባ ማህበረሰብ ተሳስበው በሚኖሩበት ላይ ሳያሰልሱ መሥራት የተሻለ እንደሆነና በማስታወቂያ ሥራ እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ማየት እንደሚገባም ይጠቁማሉ።ወንዶች ልብስ እያጠቡ ማስታወቂያ መሰራት መጀመሩን ለአብነት ያነሳሉ።በዚህ መልኩ ሴቶች በማስታወቂያ የሚሳሉበት ሁኔታ ወደፊት ይቀየራል ብለውም ተስፋ ያደርጋሉ።

አቶ ዳንኤል ብርሃኑ ለረጅም ጊዜ በጋዜጠኝነት ሰርቷል። አንዲት እናት ልጇን ስታስከትብ የሚታይበት የኩፍኝ ማስታወቂያው መርፌው ትልቅ በመሆኑ ህፃናት እንዲከተቡ የሚያበረታታ ሆኖ ባለማግኘቱ እንዲለወጥ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በግሉ ደብዳቤ በመጻፉ መርፌውና አስከታቢዋ እንዲለወጡ እስከ ማድረግ በመድረስ በመገናኛ ብዙሃን በሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ላይ በትኩረት ይሰራል።የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ሥራውን በማስታወቂያ ላይ የሰራ ሲሆን፤ በመገናኛ ብዙሃን በሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ዙሪያም መጻፎች ጽፏል።“ማስታወቂያ ሳቢ መሆን አለበት ሳቢ ለማድረግ ከምንጠቀምበት አንዱ ሴቶችን ማሳየት ነው” የሚለው ዳንኤል በማስታወቂያ ሳይንሱ ሰዎች የሚያተኩሩት ቆንጆ መልክና ቅርጽ ባላቸው ሴቶች ሁኔታ ላይ እንጂ በሚተላለፈው ምርትና አገልግሎት ባለመሆኑ ውጤታማ አይደለም ተብሎ እንደሚታመን ያወሳል። ሴቶቹ ላይ በማተኮር እንደማይገነዘቡት የሚያረጋግጡ ጥናቶች እንዳሉም ይጠቁማል። ይሄ እንደ ትምህርት ቤት አስተምረን ፈትነን ለውጡ ይሄን ያህል ነው እንደሚባለው አይደለም። ወጥ ልጇ አብራ እንድትቀምስ የምታደርግ እናት ያለችበትን ማስታወቂያ የምታይ ሴት ልጅ ወጥ መቅመስ የእናትና የሴት ልጅ ሥራ እንደሆነ አድርጋ ነው የምታስበው ተብሎ ይገመታል።ይሄም ታዳጊዎች የመጣውን አስተሳሰብ ዕውነት ነው ብለው እንዲቀበሉ ያደርጋል።

‹‹የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ሲነሳ የተለመዱ አስተሳሰቦች፤ የተለመዱ ያለፍንባቸው የኑሮ ዘይቤዎች በማስታወቂያ መደጋገማቸው ደግሞ ያፀናቸዋል፤ እንዲቀጥሉ ያደርጋል›› ይላል።ዳንኤል እንደሚለው ወደፊትም እንለውጠዋለን ብለን የምናስበውን ማህበረሰብ ለመለወጥም ማስታወቂያ ትልቅ ሚና አለው ተብሎ ይታሰባል።ሆኖም ለውጡ እንደ ትምህርት ቤት አስተምረን ፈትነን ለውጡ ይሄን ያህል ነው እንደሚባለው ሳይሆን ረጅም ጊዜ ይፈጃል። ወጥ ልጇ አብራ እንድትቀምስ የምታደርግ እናት ያለችበትን ማስታወቂያ የምታይ ሴት ልጅ ወጥ መቅመስ የእናትና የሴት ልጅ ሥራ እንደሆነ አድርጋ ነው የምታስበው። በመሆኑም ሁሉም ሴት ልጆች የመጣውን አስተሳሰብ ዕውነት ነው ብለው እንዲቀበሉ ያደርጋል።

‹‹የስርዓተ ጾታ ጉዳይ በየትኛውም መመርያዎች ውስጥ በግልጽ አልተቀመጠም›› ይላል። እንደ እሱ የስርዓተ ጾታ እኩልነት ተሳትፎ፤ ተጠቃሚነት፤ እነዚህ ከሰብዓዊ መብት፤ ከባህልና ከልማዶቻችንን ጋር እንዴት ነው የሚታዩት ሲባል የሚያከራክሩ ናቸው። ለምሳሌ አጭር ቀሚስ ምንድነው የቱ ድረስ ሲሆን ነው አጭር የሚሆነው? ራቁትነት የሚፈጠርባቸውና የማይፈጠርባቸው ብለው የሚያስቧቸው አሉ። በከፊል ራቁትነት የሚፈጠርባቸው ተቀባይነት የሚያገኘው እስከምን ድረስ ሲሆን ነው የትስ ቦታ የሚለውም ይታያል። ተገቢ ነው ወይ የሚል ጥያቄም ሲነሳ ይስተዋላል።እነዚህ ሁሉ ማስታወቂያ ሲነሳ አብረው የሚነሱ ናቸው።

‹‹ሴቶች ወደ አመራር እንዲመጡ ብዙ መመቻቸት ያለባቸው ሁኔታዎች አሉ። አንደኛው በዚህ ረገድ እኛ ለእኩል ውክልና የምንሰራበት ሴቷ መምራት ትችላለች ብሎ ማህበረሰቡ ማሰብ ያለበት መሆኑ ነው›› የምትለው በዩኤ ውሜን ሴቶችን ወደ ውሳኔ ሰጭነት የማምጣት ጉዳይ ኃላፊ ደሴት አበበ መገናኛ ብዙሃን ውስጥ ስለሴቶች ያለውን አመለካከት በዋንኛነት የሚቀርጸው ማስታወቂያ እንደሆነም ታሰምርበታለች።ደሴት ምክንያቱን ስትገልጽም አንዲት ሴት ልትመራ ስትሄድ የሚቀበላት ማህበረሰብ ከሌለ በተመደቸበት ተቋም መምራት ያቅታታል። ማህበረሰቡ ሴትን መሪ አድርጎ እንዳያይ የሚያደርግ አስተሳሰብ በእምሮው እንዲቀረጽ ከሚያደርጉት ውስጥ አንዱ በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፈው ማስታወቂያ እንደመሆኑ በመገናኛ ብዙሃን ሴቶች የሚሳሉበት በሕይወት ዘመናቸው በሙሉ የሚከተላቸው እንደሆነም ትጠቅሳለች።አሁን ላይ እየተሻሻለ ቢመጣም ሴቶች በማስታወቂያ ውስጥ የሚሳሉት በዳይፐር በወተት፤ በሳሙና፤ በምግብ ቅቤ ሁልጊዜ ከጓዳና ከቤት ውስጥ ሥራዎች ጋር በተያያዘ እንደሆነ ታነሳለች። እንደምትለው ልጅ ማሳደግ የሴት ኃላፊነት ብቻ ተደርጎ ነው የሚሳለው በማስታወቂያ። ወንዶችን ደግሞ መሪ፤ ኃላፊ፤ ውሳኔ ሰጭ፤ ባለገንዘብ አድርጎ መሳል አለ።ይሄ ደግሞ ሴቶች በፖለቲካው ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ አይደሉም፤ በኢኮኖሚው ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ አይደሉም። ቤት ነው እንጂ መሥሪያ ቤት መምራት አይችሉም፤ ቤት ነው እንጂ አገር መምራት አይችሉም የሚለውን አስተሳሰብ በተለይ በህፃናት አእምሮ እያሰረፀ ይሄዳል። አገር ተረካቢ ህፃናት ነገ ስለ ሴቶች የሚያስቡት በማስታወቂያ የሚያዩትንና የሚማሩትን ነው።በመሆኑም ይሄ አመለካከት መቀየር አለበት። ማስታወቂያ የሚሰሩ ሰዎች ሁለቱንም አመጣጥነው ነው መሳል ያለባቸው የሚል ሀሳብ ነው ያለው ዩኤን ውሜን። ከአምስት ዓመት በፊት ከመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ጋር በመተባበር የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎቹን ማሰልጠን ጀምረናልም ትላለች። በሚያሰለጥኗቸው ወቅት የማስታወቂያ ይዘትን ጥራትን የሚወስኑት እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ምርታቸው እንዲተዋወቅላቸው የሚፈልጉ ባለሀብቶችም አሉና ስልጠናው ሁሉንም ተደራሽ ማድረግ አለበት የሚል እምነት አላቸው ብላናለች።

ከዩኤን ውሜን ጋር በመቀናጀት በዚሁ ዙርያ በርካታ ሥራዎችን ስትሰራ የቆየችው በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ዳይሬክተር ዱረቲ ታደሰ እንደምትለው እሷ እንደምትሰራበት ተቋም በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ማናቸውንም ጉዳዮች የሚቆጣጠርና የሚከታተል ራሱን የቻለ የማስታወቂያ ክትትልና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት አለ።ዳይሬክቶሬቱ መገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያ ሲሰሩ ስርዓተ ጾታን እንዴት ተረድተው ነው የሚሰሩት የሚል የማስታወቂያ መመሪያ አዘጋጅቷል። ስልጠናዎችንም ይሰጣል። በዳይሬክቶሬቱ ሥር ማስታወቂያ እንዴት ሞኒተር እንደሚደረግ የሚከታተል አካል ያለ ሲሆን እሷ የምትመራው ዳይሬክቶሬትም ሴቶች በማስታወቂያ ውስጥ በሚሳሉበት አግባብ ከማስታወቂያ ክትትልና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬቱ ጋርም በቅንጅት ይሰራል።በተለይ በማስታወቂያ የሚተላለፉትን በሚቆጣጠርበት ወቅት በእሷ የሚመራው ዳይሬክቶሬትም የራሱ የክትትል አግባብ አለው። በተጨማሪም እንደ ተቋም የቅሬታና የተቃውሞ ማስተናገጃ ስርዓት የዘረጋበት 9192 የተሰኘ ስርዓት በመኖሩ ማንኛውም ሰው በመገናኛ ብዙሃን በሚተላለፉ ፕሮግራሞችና ማስታወቂያዎች ዙሪያ ያለውን ቅሬታ ያቀርባል።

‹‹አንዳንዶቹ ማስታወቂያዎች ሴቶች ከአገራችን ባህል ውጭ በሆነ መልኩ እየተገላለጡ የሚያስተዋውቁባቸው ናቸው።ሴቶች በዚህ ቦታ ላይ ለሚተዋወቀው ዕቃም ሆነ ለማስታወቂያው አስተዋጾ እንዳላቸው ሳይሆን የዕቃው አሻሻጭ ወይም እንደ ዕቃ የሚቆጠሩበት ሁኔታ አለ›› ትላለች። እንዳከለችው ይሄን ችግር ለመፍታት የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና በክትትል የተገኙ ችግሮችን መሰረት በማድረግ ማስታወቂያዎች ሞኒተር ይደረጋሉ።የማስታወቂያ ድርጅቶችን አስነጋሪዎችን የማሰልጠንና የማግባባት (የአድቮካሲ ሥራ) ይሰራል።ስልጠናው ምን እንዳገዛቸው መጠይቅ ተበትኖ የዳሰሳ ጥናት ይጠናል።በመጣው ለውጥ ላይም ክትትል ይደረጋል።በዚህ መሰረት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲያደርጉ ደብዳቤ ተጽፎላቸው ትእዛዙንም ተቀብለው ያስተካከሉ አሉ።በመሆኑም ለውጦች አሉ። ከዚህ ቀደም የሳሙና ማስታወቂያ ሲሰሩ የነበሩት ሴቶች ቢሆኑም አሁን እንዲህ ዓይነት ማስታወቂያዎች በወንዶችም እየተዋወቁ መሆኑ ማሳያ ነው።ሆኖም ማስታወቂያ ሥራ ስርዓተ ጾታን ያገናዘበና ጾታዊና ግላዊ ክብርን፤ ባህልን፤ ወግና ሐይማኖትን የጠበቀ እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ብዙ ይቀራል።በቀጣይም ብዙ ተተግቶ ሊሰራባቸው የሚገቡ አሉ።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን የማስታወቂያ ክትትልና አቅም ግንባታ ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ፋንታዬ በመገናኛ ብዙሃን ከሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ጋር ተያይዞ ባለስልጣኑ የሚሰራበት 759/2004 በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣ የአገር የማስታወቂያ አዋጅ አለ።ይሄን የሚያስፈጽመው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ሲሆን አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆነውም በአገር ውስጥ ያሉ ኢንዳስትሪ ላይ ነው። የራሳቸውን ሥራ ስርዓተ ጾታን ያገናዘበ መሆኑን የሚረዱበትና በሴቶች ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖን የሚቀንሱበት የማስታወቂያ ካውንስልም ያቋቋሙበት ሁኔታ አለ።በተጨማሪም ስርዓተ ጾታ ተኮር የማስታወቂያ ስርጭት ስታንዳርድ ወጥነት ባለው መልኩ መዘጋጀት ስላለበት ተዘጋጅቷል። የሚመለከታቸው አካላቶች ሀሳብ ሰጥተውበታል። እሱም ዳብሮ ለሚመለከተው አካል ተበትኖ ወደ ተግባር ተገብቷል። ይሄ ከዚህ ቀደም ያሉትን ክፍተት ይደፍናል ከዚህ ጋራም ብዙ ለውጦች አሉ ይላሉ።መልካም ንባብ!

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ የታተሙ ጋዜጦች የዛሬው ዓምዳችን መዳረሻ ናቸው። ከመራረጥናቸው ዘገባዎች መካከል አብዛኞቹ ልማት ተኮር ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት በአዲስ አበባ ስለሚያደርገው ስብሰባ፣ የወጣት ገበሬዎች በዓል በመቀሌ፣ ፈረንሳይ ከአዲስ አበባ ወደ ሲዳሞ የሚወስድ ባቡር መስመር ለመዘርጋት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መፈራረሟን ግማሽ ክፍለ ዘመን መለስ ብለው የሚያስታውሱ ዘገባዎችን እንድታነቡት እነሆ ብለናል።

### ከቆቃ አካባቢ ሕፃናት በሞላ ወንዝ ተወስደው ሞቱ

ናዝሬት ፤ (ኢ.-ዜ-አ-) በናዝሬት ከተማና አካባ ባለፈው ማክሰኞ የጣለው ኃይለኛ ዝናብ ያስከተለው ጐርፍ በሰውና በእንስሳት ሕይወት ላይ ጉዳት አደረሰ።

ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ ፩ ሰዓት ተኩል ድረስ በጣለው ኃይለኛ ዝናም በሎሜ ወረዳ ግዛት በቆቃ አካባቢ የሚገኘው ወንዝ ሞልቶ ፪ ሕፃናት በወህው ተወስደው ሞተዋል።

በናዝሬት ከተማም የምንጃር ጐዳና ተብሎ በሚጠራው መንገድ ግራና ቀኝ ለወሀ መውረጃ ተብሎ የተቆፈረው ቦይ ሞልቶ ፯ የቀንድ ከብቶችን ወስዷል።

እንዲሁም በከተማው ውስጥ የሚገኙት አስፋልት መንገዶች ከመጠን በላይ በጐርፍ ወሀ ተሸፍነው ተሽከርካሪዎችንና እግረኞችን ከማስቸገራቸውም በላይ፤ የጐርፉ ወሀ በአንዳንድ ቤቶች ውስጥ በመግባት ቀላል የንብረት ጉዳት ማድረሱን አንድ የአውራጃው ግዛት ፖሊስ ጽ/ቤት ቃል አቀባይ ገልጧል። (ሰኔ 21 ቀን 1964 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን )

### የወጣት ገበሬዎች በዓል በመቀሌ

መቀሌ፤ በትግሬ ጠቅላይ ግዛት በመቀሌ ከጥር ፳፬ /፶፭ ዓ ም ከቀኑ ፰ ሰዓት ጀምሮ በዐፄ ዮሐንስ ት/ቤት ቅፅር ግቢ ውስጥ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት የወጣቶች ገበሬዎች በዓል ተደርጐ ውሏል።

የበዓሉ ተካፋይ ለመሆን የመጡት እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል ንግግር ከአቶ ተክለ አብ ወልዴ ከተሰማ በኋላ፤ ስለወጣቶች ገበሬዎች ሥራ ማስረዳት ለመወዳደር ከአድዋ፤ ከአዲግራት፤ ከውቅሮ፤ ከማይጨው፤ ከኮረም የመጡትና የመቀሌ ተማሪዎች በየተራ እየተነሱ ስለችግኙ አበቃቀልና አተካከል ስለፍግ አጠባበቅ ስለጓሮ አትክልት አተካከል ዘዴና ስለዶሮ ርቢ አያያዝ ለተሰበሰበው ሕዝብ ካስረዱ በኋላ፤ በውድድር አሸናፊ ለሆኑት ፩ኛ/ለማይጨው ወጣቶች ገበሬዎች፤ ፪ኛ/ የኮረም ወጣቶች ገበሬዎች፣ ፫ኛ/ የአድዋ ወጣቶች ገበሬዎች የአሸናፊነት ሽልማት ከጠቅላይ ግዛቱ ት/ቤቶች ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በአቶ ግሩም ገብሬ እጅ ተሰጥቶ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ሲል በጠቅላይ ግዛቱ የሚገኘው ወኪላችን ባስተላለፈው ወሬ አመልክቷል። (ጥር 27 ቀን 19 55 ከወጣው አዲስ ዘመን)

### ቫልድሃይም ለፀጥታ ምክር ቤት ጉባዔ አዲስ አበባ ይመጣሉ

አዲሱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ኩርት ቫልድሃይም የድርጅቱ የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት በሚያደርገው ጉባዔ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን የድርጅቱ ቃል አቀባይ አስታወቀ። ቫልድሃይም የደርጅቱ ዋና ጸሐፊ ሆነው ከተመረጡ ወዲህ፤ ውጪ አገር ሲኀበኙ ያሁኑ የመጀመሪያቸው እንደሚሆን ተገልጧል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት አዲስ አበባ ላይ የሚሰበሰበው ከጥር ፲፱ ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፳፯ ቀን /፳፬ ዓ/ም/ ሲሆን፤ በዚሁ ጊዜ በደቡባዊው የአፍሪካ ክፍል ችግሮችና፤ እንዲሁም በቅኝ ግዛት ጉዳይ እንደሚነጋገር ታውቋል። እንዲሁም ምክር ቤቱ በአዲስ አበባ እንደሚሰበሰብ ከድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ትናንት ለመጀመሪያ ጊዜ በኦፊሴል አዲስ አበባ ለሚገኘው ለአፍሪካ ኤኮኖሚክስ ኮሚሽን ጽ/ቤት መልዕክት ተላልፏል።

አሥራ አምስት አገሮች በአባልነት የሚገኙበት የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ የሚያደርገው ስብሰባ እ/ኤ/አ/ ከ፲፱፻፵፪ ወዲህ ምክር ቤቱ ከኒውየርክ ውጪ ሲሰበሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው። ምክር ቤቱ እ/ኤ/አ/ በ፲፱፻፵፪ ዓ/ም / በፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ ላይ ስብሰባ ማድረጉ ይታወሳል። ምክር ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ምድር ላይ የሚሰበሰበው በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጠያቂነት ነው።

አዲስ አበባ ላይ በሚደረገው የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤቱ ጉባዔ ላይ ብዙ የውጪ ሊቃውንት በውይይቱ ተካፋዮች እንደሚሆኑ ሲገልጥ፤ የ፲፭ ቱ የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት አባል አገሮችም በድርጅቱ ዘንድ የሚገኙትን ዋና ዋና መልእክተኞቻቸውን እንደሚልኩ አስታውቀዋል።

የፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት በአዲስ አበባ የሚያደርገው የጉባዔ ጊዜ፤ በሮዴሺያና በእንግሊዝ መካከል የተደረገው ስምምነት ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚቀርብለትን ሀሳብ እንደሚመለከት ተገልጧል።

ሆኖም እንግሊዝ ሀሳቡን ባለፈው ወር በፀጥታ ጥበቃ ምክር ቤት ጉባዔ ላይ ድምፅን በድምፅ በማገድ ሥልጣኗ በመጠቀም መጣሏ ይታወሳል። (ጥር 10 ቀን 19 64 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን)

### የምድር ባቡር መስመር ለመዘርጋት የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ካለው የኢትዮጵያና የፈረንሳይ የምድር ባቡር መስመር አንስቶ ወደ ሲዳሞ የሚወስድ የምድር ባቡር መስመር ለመዘርጊያ የሚሆን የገንዘብ ብድር ስምምነት ኢትዮጵያና ፈረንሳይ ፓሪስ ላይ የተፈራረሙ መሆናቸውን የደረሰን ወሬ አመልክቷል።

ይህን የአምሳ አምስት ሚሊዮን ፍራንክ ብድር ስምምነት ፓሪስ ላይ የተፈራረሙት በኢትዮጵያ መንግሥት በኢትዮጵያ በኩል ክቡር አቶ ማሞ ታደሰ በጠቅላይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሲሆኑ በፈረንሳይ መንግሥት በኩል ደግሞ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ የተራድኦ አሰጣጥ ም/ሚኒስትር ሙሴ ሚሼል ሐቢብ ደ. ሎንክ ናቸው። ይህን አዲስ የምድር ባቡር መስመር ለመዘርጋት አስፈላጊውን መሣሪያ እንዲያቀርቡ የሚመደቡት የፈረንሳይ ኩባንያዎች መሆናቸውን ወሬው በድጋሚ አስታውቋል። (ሰኔ 21 ቀን 19 64 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ

## ነዳጅ አምራቾች ምርት ለመቀነስ ከተስማሙ በኋላ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አሳየ

የዓለማችን ከፍተኛ ነዳጅ አምራች አገራት ሳይጠበቅ የነዳጅ ምርትን ለመቀነስ ከተስማሙ በኋላ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አሳየ። በዚህም የአንድ በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ በ7 በመቶ Ceማሪ አሳይቶ ከ85 ዶላር በላይ እየተሸጠ ነው።



የነዳጅ ዋጋ ጭማሪው የመጣው ሳዑዲ አረቢያ፣ ኢራቅ እና ሌሎች በርካታ የባህረ ሰላጤው አገራት በቀን የአንድ ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ ምርት ቅነሳ እናደርጋለን ካሉ በኋላ ነው። ቀደም ሲል የሩሲያና ዩክሬንን ጦርነት ተከትሎ የነዳጅ ዋጋ ጨምሮ የነበረ ቢሆንም የነዳጅ ዋጋ ከጦርነቱ በፊት ወደነበረበት ተመልሶ ነበር። አሜሪካ የነዳጅ ዋጋን ለማረጋጋት አምራቾች ምርት እንዲጨምሩ ስትጠይቅ ቆይታለች።

ባለፉት ወራት የኢነርጂ እና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ የዋጋ ግሽበት በመፍጠር በመላው ዓለም የኑሮ ውድነትን ፈጥሮ ነበር። ነዳጅ አምራች አገራቱ የምርት ቅነሳ ማድረጋቸውን ካሳወቁ በኋላ የአሜሪካ ብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤት ቃል አቀባይ፤ "የገበያ መረጋጋት በሌለበት በዚህ ወቅት የምርት ቅነሳ ማድረጉ የሚመከር አይደለም - ይህን ግልጽ አድርገናል" ብለዋል።

የምርት ቅነሳውን ያደረጉት ኦፔክ+ የሚባሉት ነዳጅ አምራች አገራት ሲሆኑ ለዓለም ገበያ ከሚቀርበው የነዳጅ መጠን 40 በመቶውን ይሸፍናሉ። ሳዑዲ አረቢያ የቀን ምርቷን በ500ሺህ በርሜል የምትቀንስ ሲሆን ኢራቅ ደግሞ በ211ሺህ በርሜል የዕለት ምርቷን ትቀንሳለች። የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች፣ ኩዌት፣ አልጄሪያ፣ ኦማንና ሌሎች የምርት ቅነሳ የሚያደርጉ አገራት ናቸው።

የሳዑዲ የኢነርጂ ሚኒስቴር የነዳጅ ምርት ላይ ቅናሽ ማድረግ ያስፈለገው የነዳጅ ገበያ መረጋጋት ለመፍጠር የተወሰደ ጥንቃቄ እርምጃ ነው ስለማለቱ የሳዑዲ የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። ናታን ፓይፐር የተባሉ የዘርፉ ተንታኝ ግን ለቢቢሲ ሲናገሩ ነዳጅ አምራቾች ምርታቸውን የቀነሱት በዓለም ምጣኔ ሃብት መቀዛቀዝ ምክንያት የነዳጅ ዋጋ በበርሜል ከ80 ዶላር በታች እንዳይወርድ በማሰብ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

## ሰሜን ኮሪያ ዩክሬን ኒውክሌር የመታጠቅ ዓላማ አላት አለች

ሰሜን ኮሪያ ዩክሬን ኒውክሌር የመታጠቅ ዓላማ እንዳላት ገለጸች፡፡ የሰሜን ኮሪያ መሪ ኪም ጆንግ ኡን እህትና ጉምቱ ባለስልጣን ኪም ዮ ጆንግ ዩክሬን የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ለመታጠቅ ጥሪ አድርጋለች በማለት ክስ ሰንዝረዋል።

ኪም በፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዘለንስኪ ቢሮ በኩል ጥሪ መቅረቡንና እንቅስቃሴው የፖለቲካ ሴራ ሊሆን ይችላል ብለዋል። ሆኖም ለጉዳዩ ምንም አይነት ማስረጃ አላቀረቡም ሲል ሮይተርስ ዘግቧል። የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ባለፈው ሳምንት ታክቲካል የኒውክሌር ጦር መሳሪያን በቤላሩስ ለማስፈር እቅዳቸውን አስታውቀዋል። ይህን ተከትሎ በዩክሬን ፕሬዚዳንታዊ ጽህፈት ቤት ድረ-ገጽ ዩክሬን የኒውክሌር ጦር መሳሪያ እንድትታጠቅ የሚጠይቅ ፊርማ እየዞረ ነው ተብሏል።

የኪየቭ ባለስልጣናት ስለ ፊርማው እስካሁን በይፋ ያሉት ነገር የለም። ሰሜን ኮሪያ በምዕራቡ ዓለም የጋራ መገለል ከገጠማት ክሬምሊን ጋር የጠበቀ ግንኙነት እየፈጠረች ነው ተብሏል። ፒዮንግያንግ ሩሲያ ባለፈው ዓመት ዩክሬንን ከወረረች በኋላ የሞስኮን አቋም ደግፋለች። ሆኖም ለሞስኮ የጦር መሳሪያ ማቅረብን በሚመለከት ክሱን መካዷን አል ዐይን ዘግቧል።

የሩሲያ መንግሥት መገናኛ ብዙኃን ሩሲያ ከኔቶ ጋር ውጥረት ውስጥ መግባቷን ተከትሎ ተንታኞች ስለሞስኮ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ፉክክር አዘል ንግግሮችን ሲያደርጉ ተደምጠዋል።



# ስፖርት


## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በበርካታ የጎዳና ላይ ውድድሮች ድል ቀንቷቸዋል

**ብርሃን ፈይሳ**

በፈረንጆቹ አዲሱ ወር የመጀመሪያዎቹ ቀናት ከተደረጉት የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮች መካከል አንዱ የደቡብ ኮሪያው ዴጉ የማራቶን ውድድር ነው። ከ5 ኪሎ ሜትር እስከ ማራቶን ባሉ ርቀቶች የተለያዩ ፉክክሮችን የሚያስተናግደው ይህ የጎዳና ላይ ሩጫ ለ13ኛ ጊዜ ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች የተለመደ ድላቸውን ማጣጣም ችለዋል። በዓለም አትሌቲክስ የብር ደረጃ የተሰጠው ይህ ውድድር 15ሺ561 ሯጮችን ያሳተፈ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል ከ12 ሀገራት የተወጣጡ አትሌቶች ተካፍለውበታል። በሁለቱም ጾታዎች በተካሄደው የአርባ ሁለት ኪሎ ሜትር ውድድርም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አሸናፊዎች መሆን ችለዋል።

በወንዶች አሸናፊ የሆነው አትሌት ሚልኬሳ መንገሻ አሳማኝ በሆነ ብቃት ሌሎች የምስራቅ አፍሪካ አትሌቶችን በማስከተል ቀዳሚ ሆኖ መግባት ችሏል። ባለፉት ቅርብ ዓመታት በመም ውድድሮች የሚታወቀው ወጣቱ አትሌት ፊቱን ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች ካዞረ ወዲህ የዴጉ ማራቶን ድሉ በትልቁ የሚጠቀስ ሆኗል። አትሌት ሚልኬሳ እአአ በ2019 አህጉስ ላይ በተካሄደው የዓለም ሀገር አቋራጭ ቻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት እንደነበረም የሚታወስ ነው። ይህ ወጣት አትሌት ከተፎካካሪዎቹ በአንድ ደቂቃ ቀድሞ ድሉን ያጣጣመ ሲሆን፣ ርቀቱን የሸፈነበት ሰዓትም 2:06:49 ሆኖ ተመዝግቦለታል። በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ለሁለት ዓመታት የተሰረዘው የዴጉ ማራቶን ባለፈው ዓመት በድጋሚ ወደ ውድድር ሲመለስ በኢትዮጵያዊ አትሌት አሸናፊነት ነበር የተጠናቀቀው።

ዘንድሮ በድጋሚ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አሸናፊ በሆኑበት ሩጫም ኬንያዊው አትሌት ስታንሊ ኪፕሮቲች ሚልኬሳን ተከትሎ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል። ቀዳሚ ሆኖ ካጠናቀቀው አትሌት በአንድ ደቂቃ ዘግይቶ ውድድሩን የፈፀመው ኪፕሮቲች የገባበት ሰዓት 2:07:00 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ ኤርትራዊው ብርሃኔ ጻጋይ ደግሞ 2:07:21 በሆነ ሰዓት ውድድሩን በሶስተኝነት ማጠናቀቅ ችሏል። በሴቶች በኩል ደግሞ አትሌት አያንቱ አበራ የሀገሯን ልጅ በማስከተል ውድድሯን በአሸናፊነት አጠናቃለች። አትሌቷ 2:25:44 በሆነ ሰዓት ስትገባ፤ አትሌት መዲና ደሜ ሁለት ደቂቃዎችን ዘግይታ 2:27:27 በሆነ ሰዓት ውድድሯን ጨርሳለች። ኬንያዊቷ አትሌት ጃኔት ጊቹምቢ ደግሞ ሶስተኛውን ደረጃ ይዛለች።





**በዴጉ ማራቶን ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ሚልኬሳ መንገሻ እና አያንቱ አበራ አሸናፊዎች ሆነዋል፤**

ከዴጉ ማራቶን በተጨማሪ በሳምንቱ መጨረሻ በተለያዩ የዓለም ከተሞች በርካታ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮች የተካሄዱ ሲሆን፤ በአብዛኞዎቹ የተካፈሉት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ውጤታማ ሆነዋል። በአውሮፓ ከሚካሄዱ ማራቶኖች መካከል በጥንታዊነቱ ተጠቃሽ በሆነው የፓሪስ ማራቶን አትሌት አበጀ አያና አሸናፊ ሆኗል። ወጣቱ አትሌት በጎዳና ላይ ሩጫ ልምድ ያለውንና በዚህ ማራቶን ለአሸናፊነት ቅድመ ግምት ካገኙት መካከል አንዱ የሆነውን የሀገሩን ልጅ በማስከተልም ነው ውድድሩን የፈጸመው። በግማሽ ማራቶን ሩጫዎች በተለይ የሚታወቀው አትሌቱ ርቀቱን በአሸናፊነት ለመደምደምም 2:07:15 የሆነ ሰዓት ነው የፈጀበት።

ጠንካራ በነበረው ፉክክር በሰከንዶች ብቻ ተቀድሞ አሸናፊነትን ለጥቂት ያጣው ደግሞ ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ጉዬ አዶላ ነው። በቫሌንሺና በበርሊን ማራቶኖች የሚታወቀው አትሌቱ ለአሸናፊነት ያደረገው ብርቱ ጥረት በ20 ሰከንዶች ብቻ የዘገየ ሲሆን፤ አትሌቱ በርቀቱ ካለው ምርጥ ሰዓት ደግሞ በደቂቃዎች ዘግይቷል። እሱን ተከትሎም ኬንያዊው አትሌት ጆስፋት ቦይት በ2:07:40 ሰዓት ሶስተኛ በመሆን ገብቷል። በተመሳሳይ ጠንካራ ፉክክር በታየበት የሴቶች ሩጫም ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች አታለል አንሙት፣ ፍቅርተ ወረታ እና የሺ ቾኮለ ኬንያዊቷን ሄላ ኪፕሮፕን እጅግ ጠባብ በሆነ ልዩነት ተከትለው በመግባት ከሁለት እስከ አራት ያለውን ደረጃ መያዝ ችለዋል።

በቻይና የዚመን ማራቶንም በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ስኬታማ ሲሆኑ፤ መሰረት አበባየሁ በሴቶች አሸናፊ ልትሆን ችላለች። አትሌቷ 2:24:42 በሆነ ሰዓት ርቀቱን ስትሸፍን ተከትላት ከገባችው አትሌት የአንድ ደቂቃ ልዩነት በመፍጠር ነው። 35ሺ ሯጮች በተካፈሉበት በዚህ ውድድር ኬንያዊቷ ግላዲስ ቼሲር ሁለተኛ ስትሆን፤ በሰከንዶች ብቻ ብልጫ የተያዘባት ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት ጉተኒ ሾኔ ሶስተኛ ደረጃን መያዝ ችላለች። በወንዶች በኩል አሸናፊነቱን የተቀዳጀው ኬንያዊው አትሌት ፊሊሞን ኪፕቹምባ ኢትዮጵያዊው አትሌት ፈተና ሆኖበት ነበር። በ15 ሰከንዶች ብቻ ተቀድሞ ፉክክሩን በሁለተኝነት ያጠናቀቀው አትሌት ሌንጮ ተስፋዬ 2:08:29 የሆነ ሰዓት ማስመዝገብ ችሏል።


## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ያሬድ ገሮ ወልደሚካኤል የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-28400 የተሸከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር EAMBDANAMH0000341 ሞዴል MIE/36H/FTL/3/7.5 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0181723/0258027 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 25/7/2015 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ**
**ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ያሬድ ገሮ ወልደሚካኤል የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-94901 የተሸከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSF9HW311163 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር 1708170110I7 የሊብሬ ቁጥር 0181722/0258026 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር / ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 25/7/2015 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ**
**ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር F3-005 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0041960836 አብዱራዛቅ ሱንከሞ አምደላ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት አዲስ አበባ ቁጥር 1 መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ከቁጥር 001 እስከ 0015 የተሰራበት እና ከቁጥር 0016 እስከ 0050 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት አዲስ አበባ ቁጥር 1 መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም አብዱራዛቅ ሱንከሞ አምደላ**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስምና አድራሻ: FLORENCE COSMETICS MANUFACTURING IND. LLC አድራሻ P.O. Box 66954-Sharjah- UAE | | |
| 2 | ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀንና የማመልከቻ ቁጥር<br>የማመልከቻው ቁጥር FTM / 13558/ ቀን 2022 /7/ 9 | | |
| 3 | ምልክት: REBORN BEAUTY | 4 | የንግድ ምልክቱ ሥዕላዊ መግለጫ:- የምስል እና የቃል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 3 |
| | | | የብቸኛነት መብት ያለመጠየቅ መብት BEAUTY |
| 7 | አለም አቀፍ ምድብ.3፡ የልብስ ማጠቢያ ዝግጅቶች እና ሌሎች የልብስ ማጠቢያ አጠቃቀሞች; ማፅዳት፣ ፖሊመር ፣ መቧጠጥ እና ረቂቅ ዝግጅቶች; ያልተመደቡ ሳሙናዎች; ሽቶ፣ አስፈላጊ ዘይቶች፣ መድኃኒቶች ያልሆኑ መዋቢያዎች ፣ መድሃኒት-አልባ ፀጉር ቅባቶች; ያልተመደቡ የጥርስ ሳሙናዎች፡፡ | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፤ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል ፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOL-LXXXII No-206 26/7/2015 (4/4/2023)**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም:- ፕሪምሮዝ አገልግሎት ሰጪ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ:- ወረዳ 08 የቤት ቁጥር - ልደታ, አዲስ አበባ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር:- LTM/13838/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን:- 21/06/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት: | 4 | የምልክቱ መግለጫ:- የምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ:- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 35 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ቡና ላኪ(ምድብ 35) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን**
**ADDIS ZEMEN VOL-LXXXII No-206 26/7/2015 (4/4/2023)**